በኅብረተሰብዓዊት ኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት
በብሔራዊ አብዮታዊ የምርት ዘማቻና
የማዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ መምሪያ
የእስታቲስቲክስ ጠቅላይ ጽ/ቤት

# በገጠር የሰው ኃይል ጥናት 1973 -1974
## የመጠይቁ አሞላል መመሪያ

ጥር 29/1973

# ማውጫ

የኢስታቲስቲክስ ፡ ጠ/ጽ/ቤት ፡
ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡
C. S. O. Library

| | | ገጽ |
|---|---|---|
| I | መግቢያ | 1 |
| | 1. የጥናቱ ዓላማ........................... | 1 |
| | 2. ጥናቱ የሚሸፍነው ሥፍራና የቤተሰብ ብዛት ..... | 2 |
| | 3. ጥናቱ የሚመለከተው ጊዜ ............... | 2 |
| | 4. ጥናቱ ለማከናወን የምንጠቀምበት የጊዜ ገደብ | 2 |
| | 5. የጥናቱ መጠይቅ የሚይዛቸው መረጃዎች............... | 2 |
| | 6. ማሳሰቢያ........................... | 3 |
| II | የመጠይቁ አሞላል መመሪያ.................... | 4 |
| | ዓምድ 1 ክፍለ ሀገር......................... | 4 |
| | ዓምድ 2 አውራጃ......................... | 4 |
| | ዓምድ 3 ወረዳ......................... | 4 |
| | ዓምድ 4 ገበሬ ማኅበር ወይም የሠፈራ ጣቢያ......... | 4 |
| | ዓምድ 5 የተመረጠው ቤተሰብ መለያ ቁጥር........... | 4 |
| | ዓምድ 6 የተመረጠው ቤተሰብ ተከታታይ ተራ ቁጥር...... | 4 |
| | ዓምድ 7 የጥናቱ ዙር......................... | 5 |
| | ዓምድ 8 ጥናቱ የተከናወነበት ወርና ዓመተ ምህረት..... | 4 |
| | ዓምድ 9 ተራ ቁጥር......................... | 5 |
| | ዓምድ 10 የቤተሰብ መደበኛ አባላት ሙሉ ስም ........ | 5 |
| | ዓምድ 11 ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያለው ዝምድና......... | 6 |
| | ዓምድ 12 ጾታ......................... | 7 |
| | ዓምድ 13 ዕድሜ......................... | 7 |
| | ዓምድ 14 የትውልድ ቦታ......................... | 8 |
| | ዓምድ 15 ያለማቋረጥ እዚህ ቦታ የኖሩበት ጊዜ በዓመት... | 9 |

## ማውጫ


| | | ገጽ |
|---|---|---|
| ዓምድ 16 | የጋብቻ ሁኔታ | 10 |
| ዓምድ 17 | የቀለም ችሎታ | 10 |
| ዓምድ 18 | የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል | 10 |
| ዓምድ 19 | ባለፉት አሥራ ሁለት ወራት አብዛኛውን ጊዜ በምርታማ ሥራ ሠርተዋል ወይ ? | 11 |
| ዓምድ 20 | በዓምድ 19 መልሱ አልሠራሁም ከሆነ ያልሠሩበት ምክንያት | 13 |
| ዓምድ 21 | የሥራ ዓይነት | 14 |
| ዓምድ 22 | የቅጥር ሁኔታ | 15 |
| ዓምድ 23 | የድርጅት ዋና ምርት ወይም አገልግሎት | 15 |
| ዓምድ 24 | ባለፈው 12 ወራት ከመደበኛ ሥራቸ ተጨማሪ ሥራ ለመፈለግ ሙከራ አድርገዋልወይ ? | 18 |
| ዓምድ 25 | ሥራ በመፈለግ ሙከራ ካደረጉ በየትኛው ወራት ነበር. | 18 |
| ዓምድ 26 | ባለፉት ሰባት ቀናት ምርታማ ሥራ ሠርተዋል ወይ? | 19 |
| ዓምዓ 27 | ባለፉት ሰባት ቀናት የሠሩባቸው ቀናት ብዛት | 19 |
| ዓምድ 28 | ባለፉት ሰባት ቀናት አንድም ቀን አልሠራሁም ካሉ ያልሠሩበት ምክንያት | 19 |
| ዓምድ 29 | ሥራ አጥ ለነበሩ ያለ ሥራ የቆዩበት ጊዜ | 21 |
| ዓምድ 30 | የሥራ ዓይነት | 21 |
| ዓምድ 31 | የቅጥር ሁኔታ | 22 |
| ዓምድ 32 | የድርጅቱ ዋና ምርት የሚሰጠው አገልግሎት/ኢንዱስትሪ/ | 22 |
| ዓምድ 33 | ባለፈው ሳምንት የተከፈለው የደሞዝና የምንዳ ጠቅላላ ክፍያ | 23 |
| ዓምድ 34 | የቤተሰብ አባላት ብዛት | 23 |

III

## ማ ው ጫ


ገጽ

ዓምድ 35 የቤተሰብ ፓተርን ........................ 23

ዓምድ 36 የገበሬ ማሕበር ስም ...................... 23

ዓምድ 37 የተመረጠው ቤተሰብ መለያ ቁጥር ............. 24

ዓምድ 38 የተመረጠው ቤተሰብ ተከታታይ ተራ ቁጥር ....... 24

ዓምድ 39 ስም፣ ፊርማና ቀን ........................ 24

III የሚታወሱ ድርጊቶች የተፈጸሙባቸው ዓ.ም ................ 25

# በገጠር ለሰው ኃይል የናሙና ጥናት መጠይቅ
## አሞላል መመሪያ

## I. መግቢያ

በአንድ ሀገር የሰው ኃይል ሁኔታን በሚመለከት ዕቅድ ለማውጣት (MANPOWER PLANNING) በሀገሪቱ የሚገኘው የሰው ኃይል ብዛት ዕድሜ፣ ጾታ፣ የሥራ ዓይነት፣ ልዩ ሙያ፣ የትምህርት ደረጃ፣ በሥራ ላይ ያሉ፣ ሥራ አጥ የሆኑትንና በሥራ አጥነት የቆዩበት ጊዜ፣ በሥራ ላይ ሳሉት ከመደበኛ ቀናት በታች የሚሠሩ የሚያመለከት አስታቲስቲክስ አስፈላጊ ነው ። ይህም አስታቲስቲክስ ሊገኝ የሚችለው በሕዝብ ቆጠራ (POPULATION CENSUS) ውጤት፣ ሠራተኛን ከሥራ ጋር ለማገናኘት በሚደረገው ምዝገባ (EMPLOYMENT SERVICE INFORMATION) ውጤትና በሰው ኃይል የናሙና ጥናት (LABOUR FORCE SURVEY) ነው ።

በሕዝብ ቆጠራ ውጤት በኩል የሚገኘው አስታቲስቲክስ ስለሰው ኃይል ጥልቀት በአለው ሁኔታ ማለት ስለ ሥራ አጥና (UNEMPLOYED) በሥራ ላይ ሳሉት በሳምንት ከመደበኛ ቀናት ያነሰ የሚሠራ (UNDEREMPLOYED) ሰፋ ያለና ጥራት ያለው ሥልጠና ለመስጠት ስለማይቻል የሚገኘው አስታቲስቲክስ የተሟላ አይደለም ። እንደዚሁም ከምዝገባ የሚገኘው መረጃ በአጠቃላይ ሠራተኞችንና ሥራን በማገናኘት በኩል የሚደረገው ጥረት በፈቃደኛነት የተመሠረተ ስለሆነ፣ ምዝገባውም የሚደረገው በተወሰነ አካባቢ ብቻ ስለሆነ፣ አንድ ጊዜ የተመዘገበውን በድጋሚ የመመዝገብ ሁኔታ ስላለ፣ አብዛኛውን ጊዜ የተመዘገበውን ሥራ ፈላጊ ከሥራ አጥነት ሲላቀቅ የማያሰርዝ በመሆኑ ....ወዘተ. የሚገኘው መረጃ አብዛኛውን ጊዜ አስተማማኝና የተሟላ አይደለም ። ነገር ግን <u>በሰው ኃይል የናሙና ጥናት</u> የሚገኘው መረጃ ዝርዝር፣ አስተማማኝ፣ የተሟላና ወቅታዊም ሊሆን ይችላል ። ይኸውም ለጥናቱ የሚያስፈልጉት የመስክ ሠራተኞች የተወሰኑ ስለሆኑ ጥልቀትና ጥራት ያለው ሥልጠና ለመስጠት ከመቻሉም በላይ የሰው ኃይልን በሚመለከት ሰፋ ያለ መረጃ ለመሰብሰብ ይቻላል ። ስለሆነም በብሔራዊ የተቀናጀ የሰርቬይ ፕሮግራም ከሚጠኑት የአርሻ፣ የሶሻልና የኢኮኖሚ ነክ ጥናቶች አንዱ የሰው ኃይል የናሙና ጥናት ነው ።

## 1. የጥናቱ ዓላማ

ሀ. ለሀገሪቱ የሶሻልና የኢኮኖሚ ልማት ሊውል የሚችለውን የሰው ኃይል ብዛት ለመገመትና ስለሠራተኛ ፖሊሲ ለመተለም፣

ለ. የሠራተኛና የሥራ አጥን መጠን መገመትና ስለነሱም የሶሻል፣ ኢኮኖሚና የዲሞግራፊ ሁኔታዎችን መለየት፣ ማለትም ጾታቸውን፣ እድሜአቸውን፣ የጋብቻ ሁኔታቸውን፣ የትምህርት ደረጃቸውን .......

ሐ. ከጥናቱ የሚገኘው መረጃ የወደፊቱን /የዛሬ አምስት፣ አስር ወይም አሥራ አምስት ዓመት/ የሰው ኃይል በሥራ ዓይነትና በኢንዱስትሪ ዓይነት ለመተንበይ፣

መ. የሠራተኛንና የሥራ አጥን አስታቲስቲክስ በሚመለከት ወቅታዊ (SEASONAL) የሆነ፣ በኢኮኖሚ ዘርፍ (SECTORAL) እና በክፍለ ሀገር ያለውን ልዩነት ለመገምገም ነው ።

2. <u>የጥናቱ የሚሸፍነው ሥፍራና የቤተሰብ ብዛት</u> (Coverage) ጥናቱ የሚካሄደው በናሙና የተመረጡ 500 ገበሬ ማሕበሮችና ሠፈራ ጣቢያዎች ነው ። ጥናቱም ከነዚህ ሥፍራዎች 12,500 በናሙና የተመረጡ ቤተሰቦችን ይሸፍናል ። ጥናቱ በየክፍለ ሀገሩ ሁሉ ይካሄዳል ።

3. <u>ጥናቱ የሚመለከተው ጊዜ (frequency)</u>፡- በመጀመሪያ ጥናቱ በተመረጡት ቤተሰቦች ተካሄደ፣ ከዚያም በእነዚያ ቤተሰቦች በተከታታይ በየሶስት ወር በመደጋገም ለአንድ ዓመት /1973-74/ ይካሄዳል ። ይህ ጥናት በየሶስት ወር የሚካሄደው ወቅታዊ (SEASONAL) ለውጦችን ለመረዳትና በመጨረሻም የዓመቱን ለውጦች ለማጤን ያመች ዘንድ ነው ።

4. <u>ጥናቱም ለማከናወን የምንጠቀምበት የጊዜ ገደብ</u> (REFERENCE PERIOD) ጥናቱን ለማከናወን የምንጠቀምበት የጊዜ ገደብ እንደሚከተለው ነው ።

ሀ. መደበኛ ሥራ ሲሠራ የነበረ (USUAL ACTIVITY)

1. ጥናቱ ከመደረጉ በፊት አንድ ዓመት (LAST YEAR) በመጀመሪያው ዙር በሚካሄደው ጥናት እያንዳንዱ ዕድሜው አሥር ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆነው ግለሰብ ባለፈው አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ምን ዓይነት ሥራ ሲያከናውን እንደነበረ፣ ሥራ አጥ እንደሆነ፣ ከዚያም በተከታታይ በየሶስት ወሩ ለሚደረገው ጥናት የጊዜ ገደቡ ሶስት ወር ሆኖ የሚጠየቀው ጥናቱ ከመደረጉ በፊት ባለፉት ሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ግለሰቡ የነበረው የሥራ ሁኔታ ይሆናል ።

2. ባለፈው ሶስት ወር ውስጥ ሲሠራው የነበረ (USUAL ACTIVITY DURING THE LAST THREE MONTHS) የሚቀጥሉት በየሶስት ወር ለሚካሄዱ ዙሮች መደበኛ ሥራን በሚመለከት ባለፈው ሶስት ወር ግለሰቡ ምን ዓይነት ሥራ ሲያከናውን እንደነበረ፣ ሥራ አጥ እንደሆነ፣ ለምን ያህል ጊዜ በሥራ አጥነት እንደቆየ ።

ለ. ከአንድ ሳምንት በፊት ሲሠራው የነበረ (ACTIVITY DURING LAST WEEK OR CURRENT ACTIVITY) ማለት ጥናቱ ከመካሄዱ በፊት ባለፈው አንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ሲሠራው የነበረ የሥራ ዓይነት፣ ሥራ አጥ እንደ ነበር፣ ለምን ያህል ጊዜ በሥራ አጥነት እንደቆየ ።

5. <u>የጥናቱ መጠይቅ የሚይዛቸው መረጃዎች</u>

ሀ. ስለያንዳንዱ ቤተሰብ አባል ማኅበራዊና ዲሞግራፊአዊ ባሕርያት (SOCIAL AND DEMOGRAPHIC CHARACTERSTICS) ይጠይቃል ።

ለ. ከአሥር ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆኑ ሥራ ላላቸው ሰዎች የሥራ ዓይነት፣ የሚሠራበት ድርጅት የሚሰጠው አገልግሎት ወይም ምርት በሌላ አነጋገር ኢንዱስትሪ፣ የሠሩባቸው ቀን ብዛት፣ የአቀጣጠር ሁኔታ /ለተቀጣሪዎች/ እንዲሁም በሳምንት የተከፈላቸው ምንዳና ደሞዝ መጠን ይጠቃለላል ።

ሐ. <u>ሥራ አጥ ለሆኑት ወይም ሥራ ለሌላቸው ሰዎች</u>
ያለሥራ የቆየበት ጊዜ፣ ያገኘው የትምህርት ደረጃ ወይም ልዩ ሙያ፣ ሌሎች ማኅበራዊና ኤኮኖሚያዊ ባሕሪያትን ያጠቃልላል ::

6. <u>ማሳሰቢያ</u>

ሀ. ይህ ጥናት በየገበሬ ማሕበሩ የተመረጡ "25" ቤተሰቦችን ይሸፍናል :: እነዚህም ቤተሰቦች ለኤኮኖሚ ጥናት በፎርም ASS-3 ከተመረጡት 100 ቤተሰቦች የመጀመሪያዎቹ "25" ቤተሰቦች ናቸው :: የየዙሩም ጥናት ከተጀመረ ዕለት አንስቶ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ማጠናቀቅ ያስፈልጋል ::

ለ. አልፎ አልፎ በጥናቱ ለሚጠየቁ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት የሚችል የቤተሰቡ ኃላፊ ወይም አዋቂ የሆነ የቤተሰቡ አባል ባይገኝ ወይም በሆነ ምክንያት ቤቱ በመዘጋቱ መልስ የሚሰጥ ሳይገኝ ቢቀር የዚህ ዓይነት ቤተሰቦች ዘንድ ደጋግሞ በመሄድ የጥናቱን መጠይቅ መሙላት ያስፈልጋል :: የነዚህ ዓይነት ቤተሰቦችም ሊያገኙ ስለሚችል ጥናቱ በሚካሄድበት ሳምንት ደጋግሞ ቤተሰቡጋ በመሄድ መረጃው መሰብሰብ አለበት :: ነገር ግን ይህ ሊሆን ካልቻለ የጥናቱ ሳምንት ካለቀም በኋላ እስከ ሁለት ቀን ድረስ ቤተሰቡን በመፈለግ መጠይቁን መሙላት ያስፈልጋል ::

ሐ. የመጠይቁ ዓምድ 9 እስከ ዓምድ 34 ድረስ ስለያንዳንዱ የቤተሰብ አባል የሚጠየቅ በመሆኑ፣ ስለ ቤተሰቡ አባሎች የሚሞላው መረጃ በተቻለ መጠን በትክክል መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል ::

መ. በየዓምዱ ውስጥ መልስ ሳይሰጥበት ባዶውን የሚቀር ቦታ በየትኛው ዓምድ ውስጥ መኖር የለበትም :: ዓምዱ ለማይመለከታቸው ሰዎች ግን በየስማቸው አንጻር ሰረዝ /—/ ማድረግ አስፈላጊ ነው ::

ሠ. በመመሪያው ከተሰጡት ኮዶች በስተቀር ሌላ ኮዶች መጠቀም በጥብቅ የተከለከለ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል ::

ረ. መረጃ ሰብሳቢው ከመረጃው ሰጭ ወይም ተጠያቂው ለጥያቄዎች የሚያገኘውን መልስ ማስፈር እንጂ፣ መረጃ ሰብሳቢው ራሱ መስሎ የሚታየውን መልስ መሙላት በጥብቅ የተከለከለ ነው ::

II. <u>የመጠይቁ አሞላል መመሪያ</u>

ዓምድ 1 እስከ ዓምድ 8:- <u>ቤተሰብ የሚገኝበት ሥፍራ መለያ ዝርዝሮች ናቸው ::</u>

እነዚህ ዓምዶች ጥናቱ የሚካሄድበት የክፍለ ሀገር፣ የአውራጃ፣ ወረዳ፣ የገበሬ ማህበር ስም እና ቤተሰብ ተራ ቁጥር የሚመዘገብበት ናቸው ::

ዓምድ 1 <u>ክፍለ ሀገር</u>

ጥናቱ የሚካሄድበት የክፍለ ሀገሩ ስም ይጻፋል ::

ዓምድ 2 <u>አውራጃ</u>

ጥናቱ የሚካሄድበትን የአውራጃ ስም ይጻፋል ::

ዓምድ 3 <u>ወረዳ</u>

ጥናቱ የሚካሄድበት የወረዳ ስም ይጻፋል ::

ዓምድ 4 <u>ገበሬ ማሕበር ወይም የሠፈራ ጣቢያ</u>

ጥናቱ የሚካሄድበት የገበሬ ማሕበር ወይም የሠፈራ ጣቢያ ስም ይጻፋል ::

ዓምድ 5 <u>የተመረጠው ቤተሰብ መለያ ቁጥር /ከASS-3 ዓምድ 3 ላይ ይገኛል፣/</u>

ጥናቱ በሚካሄድበት የገበሬ ማሕበር ወይም የሠፈራ ጣቢያ ለሰው ኃይል ጥናት የተመረጡትን ቤተሰቦች ከፎርም ASS- 3 ዓምድ 3 የተሰጣቸውን የቤተሰብ መለያ ቁጥር በዚህ ዓምድ መሰፈር አለበት ::

ዓምድ 6 <u>የተመረጠው ቤተሰብ ተከታታይ ተራ ቁጥር/ከASS-3 ዓምድ 2 ላይ ይገኛል፣/</u>

ይህ ዓምድ ለጥናቱ የተመረጡትን 25 ቤተሰቦች ተራ ቁጥር እንደ አመራረጣቸው ቅደም ተከተል የሚያሳይ ነው :: ስለሆነም በመጀመሪያ ለተመረጠው ቤተሰብ "01" የሚል ተራ ቁጥር ተሰጥቶት በሁለተኛ ለተመረጠ "02" በመመዝገብ የቤተሰቦች ተከታታይ ተራ ቁጥር በዚህ ዓምድ ይሰፍራል :: ይህም ተራ ቁጥር ከፎርም ASS - 3 ዓምድ 2 ላይ ይገኛል :: የተመረጡት ቤተሰቦች ተከታታይ ተራ ቁጥር ከ"01" እስከ "25" ይሆናል ማለት ነው ::

ዓምድ 7 <u>የጥናቱ ዙር</u>

በዓመት ውስጥ ሊኖሩ የሚችሉትን ለውጦች ለመገምገም ይረዳ ዘንድ በገጠር የሰው ኃይል ጥናት ከዚህ ዙር በስተቀር በዓመት አራት ጊዜ /ዙር/ ይካሄዳል :: ስለዚህ በዚህ ዓምድ ጥናቱ ስንተኛ እንደሆነ የሚያመለክት ቁጥር ይሰፍራል :: በዚሁም መሠረት ለዚህ ዙር መለያ ቁጥር "0" አስቀድሞ የገባ ሲሆን ለሚቀጥሉት ዙሮች ማለት ለመጀመሪያው ሶስት ወር ጊዜ በኋላ ለሚካሄደው ጥናት "1" ለሚቀጥለው "2" ከዚያም "3" እያለ ለመጨረሻው ጥናት "4" ይሠፍራል ::

ዓምድ 8 <u>ወር፣ ዓመተ ምህረት</u>

በዚህ ዓምድ ጥናቱ የተካሄደበትን ትክክለኛ ወር እና ዓመተ ምህረት ይገባል ::

ዓምድ 9 <u>ተራ ቁጥር፣</u>

ይህ ዓምድ 10 ወይም ከዚህ በታች ለሆኑ የቤተሰብ አባሎችን ለመመዝገብ ተዘጋጅቷል ። ነገር ግን የቤተሰቡ አባሎች ቁጥር ከ10 በላይ ከሆነ ሌላ ተጨማሪ ፎርሞች እንደ አስፈላጊነቱ በመጠቀም በተጨማሪው ፎርም ከዓምድ 1–8 ያለውን ለክ የመጀመሪያው ፎርም በተሞላው መሠረት ይሞላል ። ከዚያም ዓምድ 9 ላይ ከዚህ በፊት የታተመውን ተራ ቁጥር 01፣ 02፣ 03፣ በመሠረዝ 11፣ 12፣ 13 በማድረግ መለወጥ አለበት ።

ዓምድ 10 <u>የቤተሰቡ መደበኛ አባላት ሙሉ ስም</u>

በቅድሚያ "ቤተሰብ" ማለት ምን ማለት መሆኑን ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልጋል፣ ቤተሰብ ማለት በአንድ ቤት ወይም በተቀራረቡ ቤቶች ውስጥ ሁልጊዜ አብረው የሚኖሩትንና ምግባቸውን በአንድ ማዕድ ቤት አብስለው በአንድነት የሚበሉትን ሰዎች ያጠቃልላል ። የቤተሰብ አባሎች በሥጋ ወይም በጋብቻ የሚዛመዱትንና የማይዛመዱትን ሊያጠቃልል ይችላሉ ። በሥጋ ወይም በጋብቻ የሚዛመዱት ባል፣ ሚስት፣ ልጆች የባል ወይም የሚስት አባት፣ እናት፣ እህት ወንድም ሲሆኑ በሥጋ ወይም በጋብቻ የማይዛመዱት የቤተሰብ አባሎችም ዘበኞች፣ የቤት ሠራተኞች፣ ጥገኞች ወዘተ.... ናቸው ።

የቤተሰብ አባላት ብዛት ሊለያይ ይችላል ። ይኸውም አንድ ሰው ብቻውን እንደ አንድ ቤተሰብ ሊቆጠር ይችላል ። ወይም ሌሎች ሰዎች እንደ ዘበኞች፣ ጥገኞች ወዘተ.... ከላይ ከተጠቀሱት ጋር የሚኖሩና በአንድነት የሚመገቡ ከሆነ እንደ አንድ ቤተሰብ ይቆጠራሉ ። ነገር ግን ጥናቱ ከሚፈጸምበት ቀን በፊት ቤተሰቡን ትቶ ለአንዳንድነት ወደ ሌላ ቤተሰብ ሄዶ ለስድስት ወር ወይም ከዚያ በላይ ከተቆጠ በኋላ አሁን ለሚገኝበት ቤተሰብ እንግዳ መሆኑ ቀርቶ ለቤተሰቡ አባል ይሆናል ማለት ነው ። ጋብቻው በአንድ ሚስት ላይ ብቻ የተመሠረተ ከሆነ አንድ ቤተሰብ ባልን፣ ሚስትን፣ ልጆችን የጉዲፈቻ ልጆችን፣ ሊያጠቃልል ይችላል ። ነገር ግን ጋብቻው ከብዙ ሚስቶች ጋር የተመሠረተ ከሆነ /ማለት አንድ ወንድ ከአንድ በላይ ሚስቶች ከአሉት/ የሰውየው ሚስቶች ከነልጆቻቸውና ዘመዶቻቸው ወዘተ... በአንድ ቤት ወይም በተቀራረቡ ቤቶች የማይኖሩ፣ ምግባቸውንም በአንድነት አብስለው የማይበሉ ከሆነ፣ እያንዳንዳቸው የሰውየው ሚስቶች እንደ ልዩ ቤተሰብ መቆጠር አለባቸው ። በዚህ ሁኔታ ባልየው አሁን ካሉቸው ከመጀመሪያ ሚስቱ ጋር እንደ ቤተሰብ አባል ሲቆጠር፣ ሁለተኛ፣ ሶስተኛ ወዘተ... ሚስቶች የየራሳቸው ቤተሰብ ሰለአሉቸው ከልጆቻቸውና ከቀሩት ጥገኞቻቸው ጋር ለየራሳቸው እንደ ቤተሰብ ይቆጠራሉ ።

ስለዚህ የቤተሰቡን ትርጉም ለይታችሁ ካወቃችሁ በኋላ የያንዳንዱን የቤተሰብ መደበኛ አባል ሙሉ ስም በዚህ ዓምድ ይጻፋል ። የቤተሰብ መደበኛ አባላት የሚባሉትም ከዚህ በታች ተመልከተዋል ።

ሀ. አብዛኛውን ጊዜ ከቤተሰቡ ጋር የሚኖሩና በቆጠራው ቀን እቤት የተገኙ ሰዎች ሁሉ እንደ አንድ ቤተሰብ አባል ይቆጠራሉ ::

ለ. አብዛኛውን ጊዜ ከቤተሰቡ ጋር እየኖሩ፣ በቆጠራው ቀን ለጥቂት ጊዜ ከቤተሰቡ የተለዩ ሰዎች ለተለዩበት ቤተሰብ አባሎች ይሆናሉ :: ለምሳሌ በዕረፍት ላይ ያሉትን፣ ለዓመት በዓል ወደሌላ ቦታ የሄዱትን፣ ዘመድ ለመጠየቅ የተጓዙትን፣ ለጥቂት ጊዜ ሆስፒታል የሚቆዩትን፣ በሥራ ምክንያት በጉዞ ላይ ያሉትን የመሳሰሉት ናቸው ::

ሐ. አብዛኛውን ጊዜ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ የሚኖሩ የቤት ሠራተኞች ዘበኞች የቀን ሠራተኞች ....ወዘተ ሌላ መኖሪያ ቤት ከሌላቸው ከሚሰሩበት ቤተሰብ ጋር አባሎች ይሆናሉ ::

መ. በአጠቃላይ አንድ ሰው ከአንድ ቤተሰብ ጋር ለስድስት ወር ወይም ከስድስት ወር በላይ ከቆየ፣ ይህ ሰው በተጠቀሰው ቤተሰብ እንደ ቋሚ ወይም የሁል ጊዜ አባል ይቆጠራል ::

ሠ. አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ ሰዎች በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ከስድስት ወር በታች የተቀመጡ ከሆነ፣ እነኚህ ሰዎች ሌላ መኖሪያ ከሌላቸው በቆጠራው ቀን ከተገኙበት ቤተሰብ ጋር አባሎች ይሆናሉ ማለት ነው :: ለምሳሌ አንዲት ሴት ልጅ አግብታ ከወላጆችዋ ቤት ተለይታ ወደ ባሏ ቤት ስትሄድ ስድስት ወር ባይሞላትም እንኳን ከባሏ ቤተሰብ ጋር መቆጠር አለባት ::

ስለዚህ በዓምድ 10 የቤተሰቡ መደበኛ አባሎች የሆኑት ሙሉ ስም በተሰጠው መስመር ይመዘገባል :: ምዝገባ በሚከናወንበት ጊዜ በመጀመሪያ መስመር የቤተሰቡ ኃላፊ፣ በሁለተኛው ሚስትን /ባልየውን/፣ በሶስተኛው ያላገቡ ልጆችን /በዕድሜ ቀደም ተከተል/፣ ቀጥሎም ያገቡ ልጆች /ከቤተሰቡ ጋር አብረው የሚኖሩ ማለት ቋሚ አባሎች ከሆኑ፣/ዘመዶቻቸውን፣ ጥገኞቻቸውን፣ ሠራተኞቻቸውን፣ ወዘተ.... ይመዘገባሉ ::

ማሳሰቢያ፣ በቅርብ ጊዜ የተወለደ ሕፃን ልጅ ካለ ሳይረሳ መመዝገብ ይገባል :: ሕፃኑ ገና ስም ያልወጣለት ከሆነ "ሕፃን" በማለት ይመዘገባል ::

ዓምድ 11 ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያለው ዝምድና፣

የቤተሰቡ ኃላፊ በሌሎች የቤተሰቡ አባላት እንደ ኃላፊ የሚታየው ሰው ነው :: የአንድ ቤተሰብ ኃላፊ በጾታ ስለማይወሰን የቤተሰቡ ኃላፊ ወንድ ወይም ሴት ሊሆን ይችላል :: በተጨማሪም ኃላፊው በቤተሰቡ ውስጥ ከሚገኙት አባሎች በዕድሜ ላይበልጥ ይችላል ::

በዓምድ 10 የቤተሰቡ አባሎች በሙሉ ከተመዘገቡ በኋላ እያንዳንዱ አባል ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያለውን ዝምድና ይገለጸ :: ስለዚህ በዓምድ 11 ለቤተሰቡ ኃላፊ "ኃላፊ" የሚል ቃል ብቻ ይጻፍለታል :: ለቀሩት ግን ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያላቸዉ ትክክለኛ ዝምድና ይገለጻል :: ለምሳሌ ሚስት/ባል፣ ወንድ ልጅ፣ ሴት ልጅ፣ እናት፣ ወንድ አያት፣ ሴት አያት ወንድም፣ እህት፣ የሚስት እህት፣ የወንድም ሚስት፣ የወንድም ልጅ፣ አክስት፣ አጎት፣ የቤት ሠራተኛ፣ ዘበኛ፣ ወዘተ.... የመሳሰሉት ናቸው ::

ዓምድ 12 <u>ጾታ</u>

ለእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል የሚከተሉትን ኮዶች በመከተል ጾታው በዚህ ዓምድ በትክክል ይሠፍራል ::

1 = ወንድ
2 = ሴት

የእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ጾታ በዓምድ 10 ከተጻፈው ስሙ/ስሟ እና <u>በዓምዱ 11</u> ውስጥ ከተገለጸው ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያለው ዝምድና ጋር መስማማቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል :: የሕፃናት ጾታ ሲመዘገብም በደንብ ማጣራት አስፈላጊ ነው ::

ዓምድ 13 <u>ዕድሜ</u>፣

ጥናቱ እስከ ተደረገበት ዕለት ድረስ የያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ዕድሜውን በጥንቃቄ በመጠየቅ በሙሉ ዓመት በዓምዱ ይመዘገባል :: ለምሳሌ አንድ ሰው ዕድሜው 13 ዓመት 11 ወር ከ3 ሣምንት ከሆነ፣ የግለሰቡ ዕድሜ 13 ዓመት ብቻ መሆኑ ይገለጸ :: የሰውየው ዕድሜ በዓመት በወርና በሳምንት የተሰጠ ከሆነ ዕድሜው በሙሉ ዓመት ብቻ ይመዘገባል :: ወደሚቀጥለው ዓመት ማጠጋት አያስፈልግም :: አንድ ሕፃን ልጅ ዕድሜው ከአንድ ዓመት በታች ከሆነ "00" ፣ አንድ ዓመት ሞልቶት ከሁለት ዓመት በታች ከሆነ ደግሞ "01" በማለት ይጻፋል :: የአንድ ልጅ ዕድሜ 2 ዓመት አልፎት ከ3 ዓመት በታች ከሆነ "02" በማለት ዕድሜው ይገለጸ፣ የቤተሰቡ አባል ዕድሜው 98 ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ "98" ይመዘገብለታል ::

የያንዳንዱን አባል ዕድሜ ለማግኘት በተቻለ መጠን መሞከር ያስፈልጋል :: ዕድሜያቸውን ለማስታወስና ለመገመት እንዲችሉ በተለያዩ ዘዴ መርዳትና ማበረታታት አስፈላጊ ይሆናል :: አንዳንድ ሰዎች ዕድሜያቸውን ለመናገር የማይፈልጉ አሉ :: እንዲያውም ስማቸው እንደተመዘገበ ካወቁ ይበልጥ ዕድሜያቸውን ለመናገር አይፈቅዱም :: ቢሆንም ከዚህ በታች የአንድን ሰው ዕድሜ ለመገመት እንዲሁም የተጠያቂዎችን ተባባሪነት ለማግኘት የሚረዱ አንዳንድ ነጥቦች ተጠቅሰዋል ::

ከቤተሰቡ አባሎች መካከል የአንዱ ዕድሜ በትክክል ከታወቀ፣ የሌሎችን ዕድሜ ለመገመት ይቻል ይሆናል :: ለምሳሌ የአንድ ቤተሰብ ትልቅ ልጅ ዕድሜው 13 ዓመት ለመሆኑ በቂ ማስረጃ ካለ፣ የእናቱ ዕድሜ ቢያንስ 28 ዓመት ብሎ ለመገመት ይቻላል :: የሥጋ ዝምድና ባላቸው

ሰዎች መካከል የአንዱን ዕድሜ ከሌላው በማነጻጸር ዕድሜያቸውን ለመገመት ይቻላል ፡፡ ለምሳሌ አብዛኛውን ጊዜ እናቶች በየሁለት ወይም በሶስት ዓመት ይወልዳሉ ፡፡ የትንሹ ልጅ ዕድሜ 7 ዓመት መሆኑን ከተረጋገጠ፣ የታላቅ ልጅ ዕድሜ 9 ዓመት ሊሆን ይችላል፡፡ ዕድሜአቸው የገፋ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ ዕድሜያቸውን በጣም ከፍ ያደርጉታል፡፡ የነኚህን ሰዎች ዕድሜ ከትልልቅ ልጆቻቸውና ከልጅ ልጆቻቸው ጋር በማነጻጸር ለመገመት ይቻላል፡፡ ስለዚህ የአንዱ ቤተሰብ አባል ዕድሜ ከታወቀ ከሌላው አባል በማዛመድ በተቻለ መጠን ትክክለኛ የሆነውን ግምት መጻፍ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም አንድ አባል ባገቡበት ጊዜ ዕድሜያቸው ስንት እንደነበረ፣ ተጋብተውም ስንት ዓመት እንደቆዩ እንደዚሁም ከልጆቻቸው ዕድሜ ጋር በማዛመድ ዕድሜያቸውን ለመገመት ይቻላል፡፡ በተጨማሪም የአንድ ቤተሰብ አባል የተወለደበትን ዓመት ከአንዳንድ ታሪካዊ ድርጊቶች ጋር በማዛመድ ዕድሜውን ለመገመት ስለሚቻል አንዳንድ ታሪካዊ ድርጊቶች የተፈጸሙበት ዓመት ዝርዝር ከዚህ መመሪያ ጋር ተያይዞ ቀርቧል፡፡

አንዳንድ ሰዎች ዕድሜያቸውን በዜሮ ወይም በአምስት በሚያልቁ አሃዞች ለመናገር ይፈልጋሉ ወይም ይቀላቸዋል፡፡ አርግጥ አንዳንድ ሰዎች ዕድሜያቸው 10፣ 15፣ 20፣ 25፣ ወዘተ..... ሊሆን ይችላል፡ ስለዚህ ዕድሜያቸውን መግለጽ የሚገባቸው ለመናገር በሚቀላቸው ወይም በሚፈልጉት ሳይሆን፣ ትክክለኛ ዕድሜያቸው መሆኑን በመገንዘብ ይህንኑ ለማግኘት መሞከር በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

ከዚህ በላይ የተሰጡትን መመሪያዎች መሠረት በማድረግ ለያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ትክክለኛውን ዕድሜ ለማግኘት ሞክሮ በዚህ ዓምድ መጻፍ አለበት፡፡

ዓምድ 14 <u>የትውልድ ቦታ፣</u>

የአንድ ሰው የትውልድ ቦታው በተወለደ ጊዜ እናቱ አብዛኛውን ጊዜ የምትኖርበትን ቦታ የሚያመለክት ነው፡፡ ለምሳሌ ሀ/ አንድ ሰው የተወለደው ሆስፒታል ውስጥ ከሆነና ሆስፒታሉም እናትየዋ አብዛኛውን ጊዜ ከምትኖርበት ቦታ ወጣ ያለ ከሆነ ለ/ ወላጂዋ የወለደችበት ቦታ እናቷ የሚኖሩበት ከሆነ ወይም ሐ/ ወላጇ የወለደችው አሌላ መንደር ከሆነ የሰውየው የሴትዮይቱ የትውልድ ቦታ እናትየው የምትኖርበት ቀበሌ ወይም መንደር መሆን አለበት እንጂ ሆስፒታሉ ያለበት መንደር፣ የእናቷ እናት የሚኖሩበት ቦታ ወይም እናትየዋ ለመውለድ ጥቂት ጊዜ የቆየችበት ቦታ መሆን የለበትም፡፡

ነገር ግን እናትዮዋ ከምትኖርበት ቀበሌ ውጭ ስድስት ወር ወይም ከዚያ በላይ ከቆየች ወይም ለመቆየት ሃሳብ ካላት የሰውየው የትውልድ ቦታ አሁን እናቱ ያለችበት ቦታ መሆን አለበት፡፡ ለምሳሌ ወይዘሮ በለጡ ከባላቸው ጋር ጤቾ አውራጃ የሚኖሩ ሆኖ ለመውለድ ከጭላሎ አውራጃ አሰላ ከተማ ቢሄዱ የልጃቸው የትውልድ ቦታ ያው ጤቾ አውራጃ መሆን አለበት፡፡ ነገር ግን አርሳቸው አዚያው አጭላሎ አውራጃ ስድስት ወር ወይም ከዚያ በላይ በራሳቸው ፈቃድ ከተቀመጡ የልጃቸው የትውልድ ቦታ ጭላሎ ይሆናል እንጂ ጤቾ አውራጃ መሆን የለበትም፡፡

ስለዚህ ዓምዱ ለያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ትክክለኛውን የትውልድ ቦታ በመጠየቅ የሚከተሉትን ኮዶች በመጠቀም ይሞላል ::

x = እዚሁ ቦታ /ጥናት በሚካሄድበት ቦታ/ ለተወለዱ
1 = ጥናት በሚካሄድበት ቦታ አውራጃ በከተማ ለተወለዱ
2 = ጥናት በሚካሄድበት አውራጃ በገጠር ለተወለዱ
3 = ጥናት ከሚካሄድበት አውራጃ ውጪ በክፍለ ሀገሩ ከተማ ለተወለዱ
4 = ጥናት ከሚካሄድበት አውራጃ ውጪ በክፍለ ሀገሩ በገጠር ለተወለዱ
5 = " " ክፍለ ሀገር ውጪ በከተማ ለተወለዱ
6 = " " " " " በገጠር ለተወለዱ
7 = በውጭ አገር /ከኢትዮጵያ ውጭ/ ለተወለዱ

የኮዱ አሞላል ከዚህ በላይ እንደተሰጠው ሆኖ ለትውልድ ቦታ በተሰጠው ክፍት ቦታ ደግሞ በተጨማሪ በቀኝ የትውልድ ቦታ በጽሑፍ ይገለጻል :: የተወለዱት እክፍለ ሃገሩ ውስጥ በከተማ ከሆነ የአውራጃውና የከተማ ስም ወይም የአውራጃውና የገጠሩ ስም ይጻፋል :: ከክፍለ ሃገሩ ውጭ ከሆነ የክፍለ ሀገሩና የከተማ ስም ወይም የክፍለ ሃገሩና የገጠሩ ስም ይጻፋል ማለት ነው ::

ዓምድ 15 <u>ያለማቋረጥ እዚሁ ቦታ የኖረበት ጊዜ ብዛት በዓመት</u>

ለእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል አሁን ባለበት ቦታ ያለማቋረጥ ስንት ዓመት እንደኖረ በመጠየቅ በዚህ ዓምድ ይሰፍራል ::

xx = ከተወለዱ ጀምሮ እስከ ጥናቱ ጊዜ ያለማቋረጥ እዚሁ ለኖሩት
00 = በገበሬው ማኅበር ያለማቋረጥ የኖሩት ከአንድ ዓመት በታች ከሆነ
01 = በገበሬው ማኅበር ያለማቋረጥ የኖሩት ከአንድ ዓመት በላይ ግን ከሁለት ዓመት በታች ከሆነ
02 = በገበሬው ማኅበር ያለማቋረጥ የኖሩት ከሁለት ዓመት በላይ ግን ሶስት ዓመት ያልሞላቸው ከሆነ
03 = በገበሬው ማኅበር ያለማቋረጥ የኖሩት ከሶስት ዓመት በላይ ግን አራት ዓመት ያልሞላቸው ከሆነ

በዚሁ መሠረት እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል በቦታው የኖረበትን የጊዜ ብዛት በሙሉ ዓመት "00"፣"01"፣ "02"፣ "03"፣ "04"፣ "05" ......."97" በዓምዱ መመዝገብ ያስፈልጋል :: ሆኖም አንድ አባል በቦታው 98 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ከኖረ 98 በዓምዱ ይገባል ::

ከዓምድ 16–25 የሰፈረት ጥያቄዎች ዕድሜያቸው አሥርና ከዚያ በላይ ለሆኑት የቤተሰብ አባላት ብቻ የሚጠየቁ ናቸው ::

ዓምድ 16 የጋብቻ ሁኔታ፣

ይህ ጥያቄ የሚቀርበው ዕድሜያቸው አሥር እና ከአሥር ዓመት በላይ ለሆኑት አባላት ብቻ ነው :: በዚህ ጥናት ስለማንም ሰው የጋብቻ ሁኔታ ማስረጃ ፍለጋና ምርምር ውስጥ ሳንገባ እያንዳንዱ ተመዝጋቢ በሚሰጠው መልስ መሠረት ብቻ የጋብቻ ሁኔታ ወይም አቋም በኮድ እንደሚከተለው ማስፈር ያስፈልጋል ::

1 = አግብተው የማያውቁ፣
2 = በጋብቻ ላይ ያሉ፣
3 = ትዳራቸው በፍቺ ምክንያት ፈርሶ ከዚያ ወዲህ ያላገቡ፣
3 = ትዳራቸው በባለቤታቸው ሞት ምክንያት ፈርሶ ከዚያ ወዲህ ያላገቡ፣

እንግዲህ እዚህ ላይ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ሚስቶች የነበሩት አንዷ ብትሞትበት ወይም አንዷን ቢፈታ ሌላ ሚስት/ሌሎች ሚስቶች/ ስለሚኖረው ባለትዳር በመሆኑ በሰውዬው ስም አንጻር በዓምዱ "2" ይጻፋል ::

የፈታት ሚስት ግን ሌላ ባል ባታገባ በጥናቱ ወቅት በፈትነት ከተገኘች በቤትዬዋ ስም አንጻር በዓምዱ "3" ይጻፋል :: ሁለት ወይም ሶስት ሴቶች አንድ የጋራ ባል ያላቸው ቢሆንም እያንዳንዳቸው በትዳር ላይ እንዳሉ ከተረጋገጠ በየስማቸው አንጻር በዓምዱ "2" መጻፍ አለበት ::

ዓምድ 17 የቀለም ችሎታ፣

ይህ ጥያቄ መቅረብ ያለበት ዕድሜአቸው 10 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑት የቤተሰብ አባላት ብቻ ነው :: ከዚህ በታች የተጠቀሱትን የቀለም ችሎታ ኮዶች በመጠቀም ትክክለኛው ኮድ በዚህ ዓምድ ይሰፍራል ::

1 = የማንበብና የመጻፍ ችሎታ ያለው፣
2 = የማንበብና የመጻፍ ችሎታ የሌለው /ማይም/፣

ዓምድ 18 የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል፣

ይህ ጥያቄ መቅረብ ያለበት ዕድሜአቸው አሥር ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑት እና በዓምድ 17 ኮድ "1" ለተሰጣቸው ማለት ማንበብና መጻፍ ለሚችሉ የቤተሰብ አባላት ነው :: እነዚህ አባላት የጨረሱት ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ እንደሚከተለው በኮድ ይገለጻል ::

00 = አንደኛ ክፍል ላልፈጸሙ፣
01 = አንደኛ ደረጃ 1ኛ ክፍል ለፈጸሙ፣
02 = " " 2ኛ " "
03 = " " 3ኛ " "
04 = " " 4ኛ " "
05 = " " 5ኛ " "
06 = " " 6ኛ " "

---

07 = መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ 7ኛ ክፍል ለፈጸሙ
08 = " " " 8ኛ " "
09 = " " " 9ኛ " "

---

10 = ሁለተኛ ደረጃ 10ኛ ክፍል ለፈጸሙ
11 = " " 11ኛ " " /አካዳሚ የፈጸሙ/
12 = " " 12ኛ " "

---

13 = የቴክኒክ ልዩ ሙያ ተቋም ውስጥ ገብተው ለፈጸሙ፣
14 = " ተቋም በመከታተል ላይ ላሉ ወይም በከፊል ተከታትለው ያቋረጡ፣
15 = የንግድ ሥራ ትምህርት ለፈጸሙ፣
16 = " " " በመከታተል ላይ ላሉ ወይም በከፊል ተከታትለው ያቋረጡ፣
17 = መምህራን ማሠልጠኛ ተቋም የፈጸሙ፣
18 = የመምህራን ማሠልጠኛ በመከታተል ላይ ያሉ ወይም በከፊል ተከታትለው ያቋረጡ
19 = ዩኒቨርሲቲ በዲግሪ ወይም በዲፕሎማ የፈጸሙ፣
20 = ዩኒቨርሲቲ ተከታትለው ያቋረጡ፣

ዓምድ 19 <u>ባለፉት አሥራ ሁለት ወራት አብዛኛውን ጊዜ በምራታማ ሥራ ተሠማርተዋል ወይ</u> ?
<u>ምርታማ ሥራ ምን እንደሆነ ማጤን ያስፈልጋል</u> ።

<u>የምርታማ ሥራ ትርጉም</u> —

ምርታማ ሥራ ማለት የሥራው ውጤት የሆነውን ሸቀጢ ሸቀጥና አገልግሎት በገንዘብም ሆነ በዕቃ በመለወጥ ገቢ ለማግኘት ለገበያ ለማቀረብ ቢቻል ነው ። ይህም በክፍያ መልክ ገቢ ለማግኘት በቀን፣ በሳምንት፣ በወር ወይም በሠሩት ሥራ መጠን ለመንግሥታዊና ለግል ድርጅቶች ወይም ለግለሰብ ሲሠሩ ነው ። በተጨማሪም በመቀጠር፣ በራስ ወይም በቤተሰብ ይዞታ በግብርና ወይም በሌላ የእርሻ ሥራ ሲሰማሩ፣ በራስ ወይም በቤተሰብ የንግድ ሥራ ሲሳተፉና ወይም በደቦ መልክ ለራስ ወይም ለሌላ ግለሰብ ሲሠሩ ነው ።

በተጨማሪም በእህል ማምረት፣ በከብትና በዶሮ እርባታ በአደንና በዓሣ ማስገር ተሰማርተው የሚገኘውን ምርት በሙሉ ለገበያ ለሽያጭ በማቀረብ ፈንታ ለቤተሰብ ፍጆታ የሚያውሉም ሥራቸው ከላይ እንደተገለጸው እንደ ምርታማ ሥራ ይቆጠራል ። ነገር ግን ከላይ ከተዘረዘሩት በስተቀር ለቤተሰብ ፍጆታ ለሚሆን የሚሰጡት አገልግሎት እንደ ምርታማ ሥራ አይቆጠርም ። ለምሳሌ የቤት እመቤት የሆነች ምግብ በማብሰል፣ ጠላ በመጥመቅና የመሳሰሉት ለቤት ውስጥ ሥራ የምታውለው ጊዜ በምርታማ ሥራ እንደ ተሰማራች አይቆጠርም ።

በዚህ መሠረት ዕድሜው አሥር ዓመትና ከዚያም በላይ ለሆናቸው ሁሉ ከላይ በተሰጠው መግለጫ መሠረት ባለፉት አሥራ ሁለት ወራት አብዛኛውን ጊዜ በምርታማ ሥራ ላይ መሰማራታቸውን ከዚህ በታች ከተመለከቱት ትክክለኛውን ኮድ በመጠቀም ዓምድ 19 ይሞላል ::

1 = አዎን ሠርቻለሁ
2 = አልሠራሁም

ይህ ዓምድ በሚሞላበት ጊዜ ከፍ ያለ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል :: ይኸውም አንዳንድ ግለሰቦች በጥቂት ጊዜያቸው እንደምርታማ ሥራ የሚቆጠር ተግባር ሲያከናውኑ በሌላ ጊዜ ደግሞ እንደ ምርታማ ሥራ በማይቆጠር ተግባር ያውላሉ :: ለምሳሌ አንዲት ሴት ወይም ሌላ የቤተሰቡ አባል ዘወትር በቤት ባልትና እና በመሳሰሉት ምርታማ ባልሆኑ ሥራዎች እየተሳተፈች በተጨማሪም አብዛኛውን ጊዜ በቤተሰቡ የእርሻ ወይም ሌላ ድርጅት ወይም የግል ድርጅት ትሠራለች :: ስለዚህ ይህች ሴት እንደ ሠራች ተቆጥራ በዚህ ዓምድ በምርታማ ሥራ እንደተሳተፈች ይመዘገብላታል :: ስለሆነም በአጠቃላይ የቤት እመቤቶችም ሆኑ ተማሪዎች አብዛኛውን ጊዜያቸው በምርታማ ሥራ በመሳተፍ የሚያውሉ ከሆነ በተባለው ጊዜ ሥራ እንደሠሩ መቆጠር ይኖርበታል ::

ዓምድ 20 <u>በዓምድ 19 መልሱ አልሠራሁም ከሆነ ያልሠሩበት ምክንያት</u> ?

አንድ ሰው ባለፉት 12 ወራት ብዙውን ጊዜ በምርታማ ሥራ ካልተሳተፈ ምርታማ ሥራ ያልሠራበትን ምክንያት የሚከተሉትን መግለጫዎች በጥንቃቄ በመረዳት ዓምዱን መሙላት ያስፈልጋል ::

1. <u>ሥራ አጥ</u>:— ሥራ ለማግኘት በመፈለግ ያሉና ሥራ ለማግኘት ጥረት ያላደረጉ ግን ሥራ ከተሰጣቸው ለሥራ ዝግጁ የሆኑትን ያጠቃልላል ::

2. <u>መደበኛ ሥራ ኖሮት በሕመም፣ በማምረቻ መሣሪያ መሰናከል ....ወዘተ ያልሠሩ</u>:—
   መደበኛ ሥራ እያላቸው በሕመም ምክንያት እንደዚሁም የማምረቻ መሣሪያቸው /ፋብሪካ፣ ትራክተር፣ የእህል መውቂያ መኪና ..../ ተሠናክሎ ባለፉት 12 ወራት ሥራ ያልሠሩትን ያጠቃልላል ::

3. <u>ተማሪ</u>:— አብዛኛው ጊዜያቸውን የአካዳሚክም ሆነ የሙያ ትምህርት በመከታተል ባለፉት 12 ወራት ያልሠሩትን ያጠቃልላል ::

4. <u>የቤት ውስጥ ሥራ ስለሚሠሩ በምርታማ ሥራ ያልተካፈሉ</u>:— ይህም በቤት ውስጥ ቤት ማጽዳት፣ ምግብ መሥራት፣ ማጠብ፣ ሕፃን ማሳደግ፣ መንከባከብ፣ ውሃ ማምጣት፣ እንጨት መሰብሰብና የመሳሰሉትን ተግባራት ብዙውን ጊዜያቸውን የሚጠፉትን ያጠቃልላል ::

5. <u>በጡረታ አበል ወይም ዘመድ ተቆራጭ በሚያደርግላቸው ስለሚተዳደሩ ያልሠሩ</u>:- በጡረታ ምክንያት ከሥራው ተገለሉ የጡረታ አበል የሚያገኙ፣ በከተማ በታና ትርፍ ቤት አዋጅ መሠረት አበል የሚያገኝ ወይም ከቤተሰብ /ከዘመድ/ በተገኘ ተቆራጭ ገንዘብ የሚ ተዳደርን ያመለክታል ::

6. <u>በአርጅና ምክንያት ያልሠሩ</u>:- በጡረታ አበል፣ ወይም በተቆራጭ ገንዘብ የማይ ተዳደሩትን ነገር ግን በዕድሜ የገፋትን ሽማግሌዎቸንና አሮጊቶቸን ያጠቃልላል ::

7. <u>አካለ ስንኩል በመሆናቸው ያልሠሩ</u>:- አካለ ስንኩል ወይም አካለ ጉደሎ በመሆናቸው ባለፈው 12 ወራት በምርታማ ተግባር ያልተሳተፉትን ግለሰቦች ያጠቃልላል ::

ስለዚህ ከላይ የተሰጡት መግለጫዎቸ መሠረት በማድረግ ከሚከተሉት ኮዶች አንዱን በመምረጥ ዓምዱ ይሞላል ::

1 = ሥራ አጥ
2 = ሥራ ኖሮት በሕመም ወይም በማምረቻ መሰናክል ያልሠሩ
3 = ተማሪ፣
4 = የቤት ውስጥ ሥራ ስለሚሠሩ በምርታማ ሥራ ያልተከፈሉ፣
5 = በጡረታ አበል ወይም ዘመድ ተቆራጭ በሚያደርግላቸው ስለሚተዳደሩ ያልሠሩ፣
6 = በአርጅና ምክንያት ያልሠሩ፣
7 = አካለ ስንኩል በመሆናቸው ያልሠሩ

ዓምድ 21 <u>የሥራ ዓይነት</u>

ይህ ዓምድ የሚሞላው ዕድሜያቸው አሥር ዓመትና ከዛ በላይ ለሆኑ፣ ባለፉት አሥራ ሁለት ወራት ውስጥ በምርታማ ሥራ ላይ በዘውን ጊዜ ለተሰማሩ ሲሆን እነኘህም በዓምድ 19 አያን ሠር ቻለሁ በለው መልስ ስጥተው ኮድ 1 ለ ተሞላላቸው ብቻ ነው :: የሥራ ዓይነት ለሚለው ጥያቄ መልስ በሚሰጥበት ወቀት ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል :: ምክንያቱም አንድ ግለሰብ ከአንድ ሥራ በላይ ሊኖረው ስለሚችል ነው :: በዚህ ዓምድ መመዝገብ ያለበት ይህ ግለሰብ አብዛኛውን ጊዜ የሚያጠፋበትንና አንደ ዋና ሥራው የሚቆጥረውን ነው ::

የያንዳንዱን የቤተሰብ አባል የሥራ ዓይነት ግልጽ በሆነ ሁኔታ መመዝገብ ያስፈልጋል :: ለምሳሌ ገበሬ፣ ከብት አርቢ፣ ደሮ አርቢ፣ ነጋዴ /የሸቀጣሸቀጥ፣ የመጠጥ፣ እህል፣ ጨርቃጨርቅ...../ ፈታይ፣ ሸማኔ፣ ልብስ ሰፊ፣ አንጥረኛ፣ ሸክላ ሠሪ፣ ቀርጫት ሠሪ፣ አናጢ፣ ለሽያጭ ምግብ አዘጋጅ፣ የሀገር ባህል መድኃኒት አገልግሎት ሰጪ፣ ወረዳ አስተዳዳሪ፣ ጸሐፊ፣ ፖሊስ፣ አስተማሪ፣ ጤና መኰንን፣ የጤና ተቆጣጣሪ፣ የሂሳብ ሠራተኛ፣ ፀጉር አስተካካይ ወዘተ... በማለት ያንዳንዱን ግለሰብ ሥራ በዝርዝር በመጠየቅ ግልጽ ባለ ሁኔታ ይሰፍራል ::

ዓምድ 22 <u>የቀጥር ሁኔታ</u>

በዓምድ 21 በተገለጸው የሥራ ዓይነት መሠረት በዚህ ዓምድ ውስጥ የግለሰቡ የቀጥር ሁኔታ ከዚህ በታች የተመለከቱትን መግለጫዎች መሠረት በማድረግ ዓምዱ ይሞላል ።

1. <u>ቀጣሪ</u>:— አንድ ሰው በግሉ የራሱን ሥራ የሚያካሂድ ከሆነና በድርጅቱ ውስጥ አንድ ወይም ከዚያ የበለጠ ሠራተኛ ቀጥሮ ሲያሠራ፣

2. <u>ተቀጣሪ</u>:— በደመወዝ ወይም በቁርጥ መልክ እየተከፈለው ተቀጥሮ የሚሠራ፣

3. <u>በግል ሥራ የሚተዳደር</u>:— አንድ ሰው በግሉ ወይም በቤተሰቡ እርዳታ ረዳትነት የራሱን ሥራ የሚያካሂድ፣

4. <u>ሳይከፈለው ለቤተሰብ ድርጅት የሚሠራ</u>:— አንድ ግለሰብ ለሚኖርበት ቤተሰብ ድርጅት ሳይከፈለው የሚሠራ፣

5. <u>በሥራ ልምምድ ላይ ያለ</u>:— አንድ ግለሰብ በአንድ ድርጅት ውስጥ ለልምምድ የሚሠራ /ለሥራው ሊከፈለው ወይም ላይከፈለውም ይችላል/ ።

ስለዚህ ከላይ የተሰጠውን መግለጫ መሠረት በማድረግ ዓምዱ ከሚከተሉት ኮዶች አንዱን በመምረጥ ይሞላል ።

1 = ቀጣሪ
2 = ተቀጣሪ
3 = በግል ሥራ የሚተዳደር
4 = ሳይከፈለው ለቤተሰብ ድርጅት የሚሠራ
5 = በሥራ ልምምድ ላይ ያለ

ዓምድ 23 <u>የድርጅት ዋና ምርት ወይም አገልግሎት /ኢንዱስትሪ/</u>

የአንድ ድርጅት /ኢንዱስትሪ/ በሚያመርተው ምርት ወይም በሚሰጠው አገልግሎት ይወሰናል ። በዓምድ 21 የሥራ ዓይነት ለተሞላላቸው ግለሰቦች ሁሉ ይህ ዓምድ ይሞላላቸዋል ። ዓምዱ ከመሞላቱ አስቀድሞ ግለሰቡ በየትኛው ድርጅት እንደሚሠራ መጠየቅ፣ ከዚያም ድርጅቱ ምን እንደሚያመርት ወይም ምን አገልግሎት እንደሚሰጥ አጣርቶ ይህንን ዓምድ መሙላት ያስፈልጋል ። ግን የሚከተሉትን ምሳሌዎች ጠንቅቆ መረዳት ዓምዱን በመሙላት ረገድ ጠቃሚ ነው ።

• የእህል ገበሬ፣ የቡና ገበሬ፣ የአትክልት ገበሬ ወዘተ.....በግል እርሻ ወይም በእርሻ ድርጅት የሚሠራ የድርጅት ውጤት የእርሻ ምርት ነው ። ስለሆነም በዓምድ 23 ምን ዓይነት የእርሻ ምርት እንደተመረተ ግለሰቡ በሚሠራበት ድርጅት ምርቱን አስፍር ።

2. ግለሰቡ በከብት ሕክምና አገልግሎት ሰጪ ድርጅት በሂሳብ ሥራ፣ በጸሐፊነት፣ በሠራተኛ አስተዳዳሪነት፣ በአትክልተኛነት፣ ወዘተ..... ከሠራ በዓምድ 23 የከብት ሕክምና ተብሎ ይመዘገባል ።

3. አንድ ግለሰብ በከብት እርባታ ድርጅት ውስጥ በሰልከኝነት፣ በአስተዳደር መኩንነት፣ በሥራ አስኪያጅነት፣ በጥበቃ ጓድነት፣ በከብት ጠባቂነት ወዘተ.... ቢሠራ በዓምድ 23 ውስጥ የከብት እርባታ ውጤት ብለህ አስፍር ።

4. አንድ ግለሰብ በአንድ የጫት ገበሬ የከብት እረኛ ሆኖ ቢቀጠር ቀጣሪው ገበሬ የሚያመርተው ጫት ስለሆነ በዓምድ 23 ውስጥ የጫት እርሻ እያልክ አስፍር ።

5. አንድ ግለሰብ በአንድ ትምህርት ቤት በመምህርነት፣ በርዕሰ መምህርነት፣ በታይፒስትነት ወዘተ....ቢሠራ፣ የድርጅቱ ውጤት የትምህርት አገልግሎት መስጠት ስለሆነ በዓምድ 23 ውስጥ የትምህርት አገልግሎት ብለህ በግለሰቡ ስም አንጻር አስፍር፣

6. አንድ ግለሰብ በአንድ ጤና ጣቢያ ወይም ሆስፒታል በነርስነት፣ በዶክተርነት፣ በሂሳብ ሥራ፣ በመዝገብ ጸሐፊነት፣ በታይፒስትነት ወይም በሌላ ሥራ የሚሠራ ከሆነ የሚሠራበት ድርጅት ውጤት ወይም አገልግሎት የጤና አገልግሎት በመሆኑ በግለ ሰቡ ስም አንጻር በዓምድ 23 የጤና አገልግሎት ብለህ አስፍር ።

7. አንድ ግለሰብ በወረዳ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት በወረዳ አስተዳዳሪነት፣ በታይፒስትነት፣ በጸሐፊነት፣ በጥበቃ ጓድነት ወዘተ.... የሚሠራ ከሆነ፣ የጽሕፈት ቤቱ አገልግሎት የወረዳ አስተዳደር አገልግሎት ስለሆነ በዓምድ 23 በግለሰቡ ስም አንጻር አስተዳደር አገልግሎት ብለህ አስፍር፣

8. አንድ ግለሰብ በጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ በማናቸውም ሥራ የሚሠራ ከሆነ በዓምድ 23 የጨርቃ ጨርቅ ምርት ብለህ አስፍር፣

9. አንድ ግለሰብ በቆዳ ፋብሪካ ውስጥ በማናቸውም ሥራ የሚሠራ ከሆነ በዓምድ 23 የቆዳ ምርት ብለህ አስፍር፣

10. አንድ ግለሰብ በማነኛውም የመንገድ ወይም ሕንፃ ፕሮጀክት ማንኛውንም የሥራ ዓይነት ከሠራ የድርጅቱ ምርት መንገድ ሕንፃ መሥራት ስለሆነ በዓምድ "23" የመንገድ እና ሕንጻ ሥራ በማለት አስፍር ።

11. አንድ ግለሰብ በቤተሰብ ድርጅት ወይም ግለሰብ ለሽያጭ የሚሆኑ ምግቦችን እያሰናዳ ከሠራ በዓምድ "23" ለሺያጭ ምግብ ማሰናዳት፣ ተብሎ ይጻፋል ።

12. አንድ ግለሰብ በቤተሰብ ድርጅት ወይም ግለሰብ ለሺያጭ የሚሆኑ የአገር ባህል መጠጦችን /ጠላ፣ ጠጅ፣ ካቲካላ ወዘተ....በማዘጋጀት ከሠራ፣ በዓምድ "23" ጠጅ፣ ጠላ፣ ለሺያጭ ዝግጅት፣ ተብሎ ይጻፍ ።

13. አንድ ግለሰብ በቤተሰብ ድርጅት ወይም ግለሰብ ተቀጥሮ ድርጅቱ የእንጨት ሥራ ውጤቶች የሆኑትን ዕቃዎች የሚሠራ ከሆነ በዓምድ "23" የእንጨት ሥራ ተብሎ ይጻፍ ::

14. አንድ ግለሰብ በራሱ ወይም በቤተሰቡ የንግድ እንቀስቃሴ ድርጅት ከሠራ ለምሳሌ በቡናና አልኮል ንግድ ቤተሰብ ድርጅት ከሆነ በዓምድ "23" ቡናና አልኮል ንግድ ብሎ መግለጽ ይኖርበታል :: ሌላም እንደ ሁኔታው የሸቀጣሸቀጥ ንግድ፣ ጨርቃ ጨርቅ፣ ምግብና ሳሙና ስኳር ጨው ዘይት ንግድ ተብሎ በመግለጽ መጻፍ ነው :: በቤት ውስጥ ተመርተው የሚሸጥ እንደ/ጠላ፣ ጠጅ፣ ካቲካላ፣ ምግብ፣ ወዘተ.... የግለሰቡ ወይም የቤተሰቡ ድርጅት እንደ "ንግድ" አይቆጠርም ስለሆነም በዓምድ "23" ለቪ ያጭ ጠጅ ካቲካላ ማስናዳት" ተብሉ ይሰፍራል ::

15. በግለሰብ ቤት ተቀጥሮ የቤት ሥራ ወይም ባልትና የሚያከናውኑ ግለሰቦች የሚሰጡት አገልግሎት የቤት ሥራ ስለሆነ በዓምዱ "23" "የቤት ሥራ" አገልግሎት ተብሎ ይጻፍ ::

16. አንድ ግለሰብ በራሱ ድርጅት ወይም በቤተሰብ ድርጅት ጋማ ከብቶች በመጠቀም መንገደኞችና ዕቃዎችን በማጓጓዝ ተሠማርቶ እንደሆነ በዓምድ "23" እንቅስቃሴ በማመልከት "የመጓጓዣ አገልግሎት" ተብሎ ይጻፍ ::

17. አንድ ግለሰብ ጐጆ ቤቶችን በመገንባት፣ የሽንት ቤት የውሃ ጉድጓድ መቆፈር ወዘተ.. የተሰማራበት የሥራ ምርት የሕንፃ ሥራ ስለሆነ በዓምድ "23" ሕንፃ ሥራ "ተብሎ ይጻፍ ::

18. ሌሎች መንግሥታዊ ድርጅቶች ለሚሠሩ ግለሰቦች በማናቸውም የሥራ ዓይነት ድርጅቶች የሚያመርቱት ወይም የሚሰጡት አገልግሎት ከዚህ በታች በጥቂቱ ተዘርዝረዋል ::

| <u>መሥሪያ ቤት</u> | <u>ምርት ወይም አገልግሎት</u> |
|---|---|
| 1. የአገር አስተዳደር ሚኒስቴር .......... | የአገር ውስጥ አስተዳደር |
| 2. ፖስታና መገናኛ ሚኒስቴር .......... | የፖስታና የቴሌፎን አገልግሎቶች |
| 3. የመንገድ ሥራ ባለ ሥልጣን .......... | መንገዶችና ድልድዮች መሥራትና መጠገን |
| 4. ሸለቆዎች ባለሥልጣን .............. | መስኖዎች መገደብና የመስኖ እርሻ ማስፋፋት |

ከዚህ በላይ የተሰጡትን ምሳሌዎች በመከተል ዓምድ 23 ይሞላ :: እዚህ ላይ የድርጅት ምርት አንድ ግለሰብ ከሚሠራው ሥራ ጋር የማይዛመድ (INDEPENDENT) መሆኑን መረዳት ጠቃሚ ነው :: የኢንዱስትሪው ተግባር የሚወሰነው በሚያመርተው ውጤት ወይም በሚሰጠው አገልግሎት ነው ::

ዓምድ 24 ባለፈው 12 ወራት ከመደበኛ ሥራ ተጨማሪ ሥራ ለመፈለግ ሙከራ አድርገዋል ወይ?

ይህ ዓምድ የሚሞላላቸው ዕድሜያቸው አሥር ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆኑ የቤተሰቡ አባላት ሲሆን በዓምድ 19 ባለፉት 12 ወራት ምርታማ ሥራ ሠርቻለሁ የሚል መልስ ሰጥተው ኮድ "1" ለተሞላላቸው፣ በዓምድ 21 የሥራ ዓይነት፣ በዓምድ 22 የቀጥር ሁኔታ በዓምድ 23 የሚሠሩበት የግል /የቤተሰብ/ ወይም መንግሥታዊ ድርጅት ዋና ምርት ወይም የሚሰጠው አገልግሎት ለተገለጸላቸው ይሆናል ። ይህም ማለት በዓምድ 19 ከምርታማ ሥራ መሳተፋቸውን በመግለጻቸው ከለም 21 — 23 ድረስ ለተሞላላቸው ብቻ ነው ።

1. ግለሰቦች ምንም እንኳን አብዛኛውን ጊዜ በምርታማ ሥራ በመሳተፍ ቢያጠፉም የተሠማሩበት ሥራ ከዓመቱ ወራት ሁሉንም ላይወስድባቸው ይችላል ። ስለሆነም ያለ ሥራ የሚቆዩበት ጊዜ ሊኖር ይችላል ።

2. ግለሰቦች ተጨማሪ ገቢ ለማግኘት ሌላ ሥራ ለመፈለግ ሙከራ ያደረጉትንም ያጠቃልላል ።

ለነዚህ ግለሰቦች ተጨማሪ ሥራ ለማግኘት ሙከራ ማድረጋቸውን ለማወቅ የሚከተሉትን ኮዶች በመጠቀም ትክክለኛው መልስ በዚህ ዓምድ ይጻፋል ።

1 = አዎን /ተጨማሪ ሥራ ለመፈለግ ሙከራ አድርጌአለሁ/
2 = አላደረጉም /ተጨማሪ ሥራ ለመፈለግ ሙከራ አላደረኩም/

ዓምድ 25 ሥራ በመፈለግ ሙከራ ካደረጉ በየትኛው ወራት ነበር ?

ይህ ዓምድ የሚሞላላቸው በተጨማሪ ገቢ ለመግኘት ሌላ ሥራ ለመፈለግ ሙከራ ያደረጉ ብቻ ስለሆነ ይህም ማለት "ከዓምድ 24" ኮድ 1 ለተሞላላቸው ነው ።

በየትኛው ወራት ለሌላ ሥራ ለመፈለግ ሙከራ አድርገው እንደነበረ ጠይቀህ ትክክለኛውን መልስ የሚከተሉትን ኮዶች በመምረጥ በዓምዱ ይሰፍራል ።

1 = ከጥር እስከ መጋቢት ያለው ሶስት ወር ጊዜ
2 = ከሚያዝያ እስከ ሰኔ ባለው ሶስት ወር ጊዜ
3 = ከሐምሌ እስከ መስከረም ባለው ሶስት ወር ጊዜ
4 = ከጥቅምት እስከ ታህሣሥ ባለው ሶስት ወር ጊዜ
5 = ከጥር እስከ ሰኔ ባለው ስድስት ወር ጊዜ
6 = ከሐምሌ እስከ ታህሣሥ ባለው ስድስት ወር ጊዜ
7 = ከጥር እስከ ታህሣሥ ባለው 12 ወር ጊዜ

ዓምድ 26 – 33 <u>እነዚህ ዓምዶች የሚሞሉት ዕድሜያቸው አሥር ዓመትና ከዛ በላይ ለሆኑ የቤተሰቡ አባላት ብቻ ሲሆን፣ ዓምዶቹም የሚያመለክቱት ስለቤተሰቡ አባላት ባለፈት ሰባት ቀናት የነበረውን የሥራ ሁኔታ ነው ።</u>

ዓምድ 26 <u>ባለፈት ሰባት ቀናት ምርታማ ሥራ ሠርተዋል ወይ</u> ?

ቀደም ብሎ በዓምድ 19 በተገለጸው የምርታማ ሥራ ትርጉም መሠረት ዕድሜያቸው አሥር ዓመትና ከዛ በላይ ለሆኑት የቤተሰብ አባላት ባለፈት ሰባት ቀኖች ውስጥ ቢያንስ ግማሽ ቀን መሥራታቸውን በመጠየቅ ይህ ዓምድ የሚከተሉትን ኮዶች በመጠቀም ይሞላል ።

1 = ሠራሁ /ግማሽ ቀን እና ከዛ በላይ ለሠሩት/
2 = አልሠራሁም /ከግማሽ ቀን በታች ወይም ጨርሶ ላልሠሩት/

ዓምድ 27 <u>ባለፈት ሰባት ቀናት የሠሩባቸው ቀኖች ብዛት፣</u>

ይህ ዓምድ የሚሞላው ባለፈት ሰባት ቀናት ቢያንስ ግማሽ ቀን ወይም ከዚያ የበለጡ ቀናት በመሥራት "ሠራሁ" የሚል መልስ ለሰጡ ግለሰቦች ብቻ ነው ። ይህም ማለት በዓምድ 26 ላይ ኮድ 1 ለተሞላላቸው ግለሰቦች ይሆናል ። ስለዚህ በዚህ ዓምድ ከጥናቱ ቀን አስቀድሞ በነበሩት ሰባት ቀናት ውስጥ ጠቅላላ የተሠራባቸው ቀናት ይሞላል ። በዚህ ዓምድ ሊሞሉ የሚችሉት ከሚከተሉት አንደኛው ሲሆን ይኸውም 1 ቀን 2 ቀናት፣ 3 ቀናት፣ 4 ቀናት፣ 5 ቀናት፣ 6 ቀናት ወይም 7 ቀናት ናቸው ። ይኸውም ዝቅተኛው 1 ቀን ሲሆን ከፍተኛው ደግሞ 7 ቀናት ይሆናል ማለት ነው ። አንድ ግለሰብ ግማሽ ቀን ወይም አንድ ቀን ከሠራ አንድ ቀን ሙሉ እንደሠራ ይቆጠርለታል፣ አንድ ቀን ከግማሽ ቀን ከሠራ እንደ ሁለት ቀን ይቆጠርለታል ። ለምሳሌ አንድ ገበሬ ከጠዋት እስከ ምሳ ሰዓት ወይም ከምሳ ሰዓት እስከ ማታ ሠራሁ ሊል ስለሚችል ይህ ገበሬ ግማሽ ቀን የሠራ መሆኑን ለመረዳት ይቻላል ። ስለዚህ ይህ እንደ አንድ ቀን ሥራ እንዳከናወነ ይመዘገብለታል ። እንደዚሁም ከጠዋት እስከ ማታ በመሥራት አንድ ቀን ሙሉ ከሠራም እንደ አንድ ቀን እንደሠራ ይመዘገብለታል ።

ዓምድ 28 <u>በዓምድ 26 ባለፈት ሰባት ቀናት አንድም ቀን አልሠራሁም ካሉ ያልሠሩበት ምክንያት</u>

ይህ ዓምድ የሚሞላው ባለፈት ሰባት ቀናት ፈጽሞ ባለመሥራታቸው ወይም ከግማሽ ቀን ያነሰ በመሥራታቸው አልሠራሁም የሚል መልስ ለሰጡት ነው ። ይህም በዓምድ 26 ኮድ 2 የተሞላላቸውን ግለሰቦች የሚመለከት ነው ። ግለሰቡ/ግለሰቧ ያልሠሩበትን ምክንያት በመጠየቅ ከሚከተሉት ኮዶች ትክክለኛ የሆነው አንዱ በዓምዱ ይገባል ።

1. <u>ሥራ አጥ፣</u> ሥራ ለማግኘት በመፈለግ ያሉና ሥራ ለማግኘት ጥረት ያላደረጉ ግን ሥራ ከተሰጣቸው ለሥራ ዝግጁ የሆኑትን ያጠቃልላል ::
2. <u>መደበኛ ሥራ ኗሮት በሕመም፣ በማምረቻ መሣሪያ መሰናከል ወዘተ. ያልሠሩ</u> – ባለፉት ሰባት ቀናት መደበኛ ሥራ እያላቸው በሕመም፣ በማምረቻ መሣሪያዎች መሰናከል /ፋብሪካ፣ ትራክተር፣ እህል መውቂያ ወ.ዘ.ተ.. ተሰናከሉ/ ያልሠሩ፣
3. <u>ተማሪ፣</u> አብዛኛውን ጊዜያቸውን የአካዳሚክም ሆነ የሙያ ትምህርት በመከታተል ባለፉት 1 ሣምንት ያልሠሩትን ያጠቃልላል፣
4. <u>የቤት ውስጥ ሥራ ስለሚሠሩ በምርታማ ሥራ ያልተካፈሉ</u> – ይህም በቤት ውስጥ ሥራ ቤት ማጽዳት፣ ምግብ መሥራት፣ ማጠብ፣ ሕፃናትን ማሳደግ፣ መንከባከብ፣ ውኃ ማምጣት፣ እንጨት መሰብሰብና የመሳሰሉትን ተግባራት ብዙውን ጊዜያቸውን የሚያጠፉትን ያጠቃልላል፣
5. <u>በጡረታ አበል ወይም ዘመድ ተቀራጭ በሚያደርጉላቸው ስለሚተዳደሩ ያልሠሩ</u> – በጡረታ ምክንያት ከሥራው ተገለሉ የጡረታ አበል የሚያገኙ፣ በከተማ በታና ትርፍ ቤት አዋጅ መሠረት፣ አበል የሚያገኝ ወይም ከቤተሰብ /ከዘመድ/ በተገኘ ተቀራጭ ገንዘብ የሚ ተዳደርን ይመለከታል፣
6. <u>በእርጅና ምክንያት ያልሠሩ</u> – በጡረታ አበል፣ ወይም በተቀራጭ ገንዘብ የማይ ተዳደሩትን ነገር ግን በዕድሜ የገፉትን ሽማግሌዎችንና አሮጊቶችን ያጠቃልላል፣
7. <u>አካለ ስንኩል በመሆናቸው ያልሠሩ</u> – አካለ ስንኩል ወይም አካለ ጉደሎ በመሆናቸው ባለፈው ሰባት ቀናት በምርታማ ተግባር ያልተካተፉትን ግለሰቦች ያጠቃልላል፣
8. <u>ጊዜያቱ የእርሻ ወቅት ስላልሆነ ሥራ ያልሠሩ</u> – የእርሻ ሥራ ጠባይ አንዳንድ ጊዜ /ለምሳሌ በእርሻ፣ በዘር፣ በአጨዳ፣ ....../ በጣም ሥራ የሚበዛ ሲሆን በሌላ ጊዜ ደግሞ በእርሻ አካባቢ የሚሠራ ብዙ ሥራ የለም /ለምሳሌ ከአጨዳ በኋላ/ :: ስለዚህ ባለፉት ሰባት ቀናት ጊዜያቱ የእርሻ ወቅት ስላልነበረ ያልሠሩትን ያጠቃልላል ::

ስለዚህ ከላይ የተሰጡትን መግለጫዎች መሠረት በማድረግ ከሚከተሉት ኮዶች አንዱን በመምረጥ ዓምዱ ይሞላል ::

1 = ሥራ አጥ
2 = ሥራ ኗሮት በሕመም ወይም በማምረቻ መሰናከል ያልሠሩ
3 = ተማሪ
4 = የቤት ውስጥ ሥራ ስለሚሠሩ በምርታማ ሥራ ያልተካፈሉ
5 = በጡረታ አበል ወይም ዘመድ ተቀራጭ በሚያደርጉላቸው ስለሚተዳደሩ
6 = በእርጅና ምክንያት ያልሠሩ
7 = አካለ ስንኩል በመሆናቸው ያልሠሩ
8 = ጊዜያቱ የእርሻ ወቅት ስላልሆነ ሥራ ያልሠሩ

ዓምድ 29 ያለ ሥራ የቆየበት ጊዜ፣

ይህ ዓምድ የሚሞላው ባለፉት ሰባት ቀናት ሥራ አጥ በመሆናቸው የተነሳ አለመሥራታቸውን ለገለጹ ሲሆን፣ እነዚህም ሥራ ለማግኘት በመፈለግ ላይ ሊሆኑ ሥራ አይገኝም በማለት ሥራ ለመፈለግ ጥረት ያላደረጉ ግለሰቦችን ያጠቃልላል ። ስለዚህ ይህ ዓምድ የሚሞላው በዓምድ 28 ላይ ኮድ "1" ለተሞላላቸው ግለሰቦች ስለሆነ ግለሰቡ ያለሥራ /ሥራ አጥ ሆኖ/ የቆየበትን የጊዜ ብዛት በመጠየቅ የሚከተሉትን ኮዶች በመጠቀም ዓምዱ ይሞላል ።

1 = ከአንድ ወር በታች
2 = ከአንድ እስከ ሦስት ወር
3 = ከአራት እስከ ስድስት ወር
4 = ከስድስት ወር በላይ.

ዓምድ 30 – 33 – በዓምድ 27 አንድ ቀንና ከዚያ በላይ መሥራታቸውን በመግለጻቸው በዓምዱ ከአንድ እስከ ሰባት ቀን የተሞላላቸውን ግለሰቦች የሚመለከት ነው ።

ዓምድ 30 የሥራ ዓይነት/ሥራው

ይህ ዓምድ የሚሞላላቸው ባለፉት ሰባት ቀናት ግማሽ ቀን በመሥራታቸው እንደ አንድ ቀን የሠሩ መሆኑ ለተመዘገባቸውና አንድ ቀንና ከዚያ በላይ መሥራታቸውን ለገለጹ ግለሰቦች ነው ። ለነዚህ ግለሰቦች ባለፉት ሰባት ቀናት የሠሩት ዋና ሥራ እላቸው ። ስለዚህ ዋና ሥራቸውን በመጠየቅ በዓምዱ ይሰፍራል ። ይህን ዓምድ በጥንቃቄ መሙላት ስለሚያስፈልግ የሥራው ዓይነት በትክክል ተገልጾ መጻፍ አለበት ። ለምሳሌ ገበሬ፣ ከብት አርቢ፣ የጤና መኮንን፣ የጤና ረዳት፣ የጤና ተቆጣጣሪ፣ የሕክምና ዶክተር እያለ እንደሥራው ዓይነት በግልጽ ይሰፍራል ። ለዝርዝሩ ዓምድ 21 መመልከት ያስፈልጋል ።

<u>በዚሁ ዓምድ /30/ የሚመዘገበው ባለፉት ሰባት ቀናት ማለትም ጥናቱ ከመደረጉ በፊት ባሉት ሰባት ቀናት ውስጥ ግለሰቡ የሠራውን ሥራ ሲሆን በዓምድ 21 የሚመዘገበው ግን ባለፉት 12 ወራት ግለሰቡ የነበረውን መደበኛ የሥራ ዓይነት መሆኑን መረዳት ጠቃሚ ነው ።</u>

<u>በዓምድ 21 ለግለሰቡ የተሞላው የሥራ ዓይነት በዓምድ 30 ከሚሞላው ጋር ተመሳሳይ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል ።</u>

በዓምድ 21 የተሞላው የግለሰቡ መደበኛ የሥራ ዓይነት በዓምድ 30 ከተሞላው የግለሰቡ የጊዜው የሥራ ዓይነት የሚለያይበትን ሁኔታ እንመልከት ። ለምሳሌ የአንድ ግለሰብ ባለፉት 12 ወራት መደበኛ ሥራው ገበሬ ነው ብንል በዓምድ 21 ገበሬ ብለን እንሞላለን ። ነገር ግን ባለፉት ሰባት ቀናት ጨርቃ ጨርቅ ይሸጥ ነበር እንበል ። ስለዚህ ባለፉት ሰባት ቀናት ግለሰቡ የነበረው የጊዜው የሥራ ዓይነት ጨርቃ ጨርቅ መነገድ ስለሆነ በዓምድ 30 ጨርቃ ጨርቅ ነጋዴ ብለን እንሞላለን ማለት ነው ።

እንደዚሁም የአንዲት ሴት ባለፉት 12 ወራት መደበኛ ሥራዋ ጠላ ጠምቆ መሸጥ ነበረ ። በዓምድ 21 ጠላ ሻጭ የሚል የሥራ ዓይነት ይመዘገብላታል ማለት ነው ። ይህችው ሴት ደግሞ ባለፉት ሰባት ቀናት ባሏን በግብርና ሥራ ትረዳው ነበር ብንል በዓምድ 30 ገበሬ ብለን እናስፍርላታለን ማለት ነው ። በጊዜው የነበረው የሥራ ዓይነትና መደበኛው የሥራ ዓይነት የሚለይበትን ለማመልከት ከጨማሪ ምሳሌ መስጠት ይቻላል ። ስለዚህ ባለፉት 12 ወራት የግለሰቡን መደበኛ የሥራ ዓይነትና ባለፉት ሰባት ቀናት ሲሠራው የነበረውን የሥራ ዓይነት መለየት ያስፈልጋል ።

ዓምድ 31 <u>የቅጥር ሁኔታ</u>

ይህ ዓምድ በዓምድ 30 እንደተገለጸው ሁሉ ግለሰቡ ወይም ግለሰቧ ባለፉት ሰባት ቀናት ውስጥ ባከናወኑት የሥራ ዓይነት መሠረት በዓምድ 22 የተሰጠውን መግለጫና ኮዶች በመጠቀም የቅጥር ሁኔታው ይሞላል ይኸውም:-

1 = ቀጣሪ
2 = ተቀጣሪ
3 = በግል ሥራ የሚተዳደር
4 = ሳይከፈለው ለቤተሰብ ድርጅት የሚሠራ
5 = በሥራ ልምምድ ላይ ያለ

ዓምድ 32 <u>የድርጅት ዋና ምርት ወይም የሚሰጠው አገልግሎት /ኢንዱስትሪ/</u>

ይህ ዓምድ የሚሞላው ባለፉት ሰባት ቀናት ውስጥ ቢያንስ አንድ ቀን በመሥራታቸው በዓምድ 30 የሥራ ዓይነት ለተሞላላቸውና እንደዚሁም በዓምድ 31 የቅጥር ሁኔታ ለተገለጸላቸው ግለሰቦች ብቻ ነው ። ስለዚህ በዚህ ዓምድ ግለሰቡ በሚሠራበት ድርጅት ዋና የምርት ወይም የሚሰጠው አገልግሎት ይመዘገባል ።

ግለሰቡ ባለፉት 12 ወራትና ባለፉት ሰባት ቀናት የሠራበት ድርጅት አንድ ከሆነ፣ በዓምድ /32/ የሚሞላው የድርጅት የምርት ውጤት ወይም የሚሰጠው አገልግሎት በመሆኑ በዓምድ 23 ከተሰጠው መልስ ጋር አንድ ይሆናል ። ነገር ግን ባለፉት 12 ወራትና ባለፉት ሰባት ቀናት ግለሰቡ የሠራባቸው ድርጅቶች የተለያዩ ከሆነ ባለፉት 12 ወራት የሠራበት ድርጅት ዋና ምርት ወይም የሚሰጠው አገልግሎት ባለፈው ሳምንት ከሠራበት ድርጅት ዋና ምርት ወይም ከሚሰጠው አገልግሎት ይለያያል ።

ለምሳሌ አንድ ግለሰብ ባለፉት 12 ወራት በዙውን ጊዜ ገበሬ ሆኖ ከሠራ፣ ሥራው በሚለው ዓምድ ገበሬ ተብሎ ይመዘገባል ። ስለዚህ የገበሬው ምርት ጥራጥሬ ስለሆነ በኢንዱስትሪ ዓምድ ውስጥ የጥራጥሬ አምራች ተብሎ ይመዘገባል ። ስለሆነም ኢንዱስትሪው የጥራጥሬ ምርት ወይም የእርሻ ምርት ነው ። ግን ግለሰቡ ባለፉት ሰባት ቀናት በቤተሰብ ድርጅት ውስጥ በሸማኔነት የሠራ ከሆነ ሥራው በሚለው ዓምድ ውስጥ ሸማኔ ተብሎ ይመዘገባል ። የድርጅቱ ምርት ጨርቃ ጨርቅ ስለሆነ ደግሞ ኢንዱስትሪ በሚለው ዓምድ ውስጥ የጨርቃ ጨርቅ ምርት ተብሎ ይሞላል ።

ዓምድ 33 <u>ባለፈው ሳምንት የተከፈለው የደሞዝና የምንዳ ጠቅላላ ክፍያ፤</u>

ይህ ዓምድ የሚሞላው በምርት ሥራ ላይ በደሞዝ ተቀጥሮ ለሚሠራና በሥራ ልምምድ ላይ ግለሰብ ነው ። ይህ ማለትም የቀጥር ሁኔታቸው በዓምድ /33/ ኮድ 2/ ተቀጣሪ ወይም /ኮድ 5/ በልምምድ ላይ ያለ የሚል ኮድ ለተመለከተላቸው ግለሰቦች ነው ።

በዚህ ዓምድ ባለፉት ሰባት ቀናት ግለሰቡ ያገኘው ጠቅላላ ክፍያ ወይም ገቢ በኢትዮጵያ ብር ይገባል ።

ይህም ዓመድ ሲሞላ የሚቀጥሉትን ነጥቦች ማስተዋል ያስፈልጋል:–

1. ምንዳና ደመወዝ በየሳምንቱ የሚከፈል ከሆነ፤ ግለሰቡ ባለፉት ሰባት ቀናት ያገኘው ጠቅላላ ምንዳና ደመወዝ በዓምዱ ይገባል፤

2. ምንዳና ደመወዝ በየወሩ የሚከፈል ከሆነ ጠቅላላ ምንዳውንና ደመወዙን በ30 አከፍሎ ውጤቱን በ7 አባዝቶ የሳምንቱ ምንዳና ደመወዝ በዓምዱ ይገባል ።

3. ጠቅላላ ምንዳና ደመወዝ በየዓመቱ የሚከፈል ከሆነ ጠቅላላ ምንዳውንና ደመወዙን በ52 ሳምንታት አከፍሎ ውጤቱ በዚህ ዓምድ ይገባል ።

4. ቋሚ ያልሆነ የደመወዝ አከፋፈል ላለው ግለሰብ የተከፈለውን ሂሣብና ክፍያ የተደረገባቸውን ቀናት ተረድቶ የአንዱን ቀን ክፍያ ጠቅላላ የተከፈለውን ክፍያ በተደረገባቸው ቀኖች ብዛት አካፍሎ ውጤቱ በሰባት አባዝቶ ውጤቱን በዚህ ዓምድ ማስገባት ነው ።

5. ምንዳና ደመወዝ በዓይነት የሚከፈል ከሆነ የተቀበለውን የዕቃዎች ዓይነት መጠን በሙሉ በመጠየቅና በሌላ ወረቀት በመመዝገብ የያንዳንዱን ዕቃ ዋጋ በአካባቢው ባለው የችርቻሮ ዋጋ መሠረት በማስላት ውጤቱን/ጠቅላላ ዋጋው በብር ይመዘገባል ።

ዓምድ 34 <u>የቤተሰብ መጠን/ጠቅላላ የቤተሰብ አባላት ብዛት/</u>

ለእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል አምዶቹ በሙሉ በትክክል መሞላቱ ከተረጋገጠ በኋላ በዓምድ 10 እና በዓምድ 12 የተሞላውን ተመልክቶ የቤተሰቡን አባላት ብዛት በጾታ በመለየት በዓምድ 34 ማስገባት ያስፈልጋል ።

ዓምድ 35 <u>የቤተሰብ ፓተርን፤</u>

ይህ ዓምድ የሚሞላው በዋና መሥሪያ ቤት ስለሆነ ባዶውን መተው ያስፈልጋል ።

ዓምድ 36 <u>የገበሬ ማሕበር ስም</u>

በዚሁ ዓምድ የገበሬ ማሕበር ስም ይጻፋል ። መጠይቁ ሁለት ገጾች ስለሚያቀፍ የገበሬ ማሕበሩ ስምም በሁለቱም ገጾች መጻፍ ስለሚኖርበት በፎርሙ በአንደኛው ገጽ በዓምድ 4 ያሰፈረውን የገበሬ ማሕበር ወይም የሰፈራ ጣቢያ ስም በዚህ ዓምድ መተላለፍ ይኖርበታል ።

ዓምድ 37 <u>የተመረጠው የቤተሰብ መለያ ቁጥር</u>

በዚሁ ዓምድ የቤተሰቡ መለያ ቁጥር ይጻፋል ። ይህም ከፎርሙ ገጽ 1 ዓምድ 5 ይገኛል ።

ዓምድ 38 <u>የተመረጠው የቤተሰብ ተከታታይ ተራ ቁጥር</u>

በዚሁ ዓምድ የቤተሰቡ ተከታታይ ተራ ቁጥር ይጻፋል ። ይህም ከመጠይቁ ገጽ 1 ዓምድ 6 ይገኛል ።

ዓምድ 39 <u>ስም ፊርማና ቀን፣</u>

ይህ ዓምድ መረጃ ሰብሳቢው፣ የመስክ ተቆጣጣሪውና የክፍለ ሀገሩ የእስታቲስቲክስ ኃላፊ ጥናቱ በትክክል መከናወኑን ለማረጋገጥ ስማቸውን፣ ፊርማቸውንና እንደዚሁም ቀን የሚሰፍሩበት ነው ። ስለዚህ መረጃ ሰብሳቢዎች ሥራው በትክክል መሠራቱን ለማረጋገጥ ለያንዳንዱ ቤተሰብ ፎርሙን ከሞሉ በኋላ ስማቸውን መጻፍና በመፈረም ይህም የተደረገበትን ቀን እንዲያመለክቱ ያስፈልጋል ። እንደዚሁም የመስክ ተቆጣጣሪዎች መረጃው በተሰጠው መመሪያ መሠረት መሰብሰቡን አይተው ማረጋገጣቸውን ለማመልከት ስማቸውን በመጻፍ፣ ፊርማቸውንም ማስፈር ይህም ተግባር የተከናወነበትን ቀን እንዲመዘግቡ ያስፈልጋል ። በመጨረሻም የክፍለ ሀገሩ የእስታቲስቲክስ ክፍል ኃላፊ መረጃ ሰብሳቢውም ሆነ የመስክ ተቆጣጣሪው ሥራቸውን በትክክል ማከናወናቸውን ለማረጋገጥ ስሙን፣ ፊርማውንና ቀኑን ማስፈር አለበት ።

## የቤተሰቡ አባላት ዕድሜአቸውን እንዲያስታውሱ የሚረዱ የሚታወሱ ድርጊቶች የተፈጸሙበት ዓመትና እስከ 1973 ዓ.ም ድርጊቱ ከሆነ ያለፈው ዘመን ብዛት:-

| የሚታወሱ ድርጊቶች | ድርጊቱ የተፈጸመበት ዓ.ም | ድርጊቱ ከተፈጸመበት ጊዜ እስከ 1973 ዓ.ም የዓመቱ ብዛት |
|---|---|---|
| 1. አጼ ዮሐንስ አረፉ /የመተማ ጦርነት/ | 1881 | 92 |
| 2. አጼ ምኒልክ ነገሡ | 1882 | 91 |
| 3. ዙፋይ የተመታበት | 1886 | 87 |
| 4. የወላም ዘመቻ | 1887 | 86 |
| 5. የአድዋ ዘመቻ | 1888 | 85 |
| 6. አጼ ምኒልክ አረፉ/ልጅ እያሱ ነገሡ | 1906 | 67 |
| 7. ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ነገሡ ወይም ሠገሌ ጦርነት | 1909 | 64 |
| 8. አቴጌ ጣይቱ አረፉ | 1910 | 63 |
| 9. የሕዳር በሽታ | 1911 | 62 |
| 10. ልጅ ኢያሱ የተያዙበት | 1013 | 60 |
| 11. ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ አረፉ/አቡነ ማቴዎስ አረፉ/ | 1919 | 54 |
| 12. የማይጠው ጦርነት | 1982 | 45 |
| 13. የኢትዮጵያ ሰማዐታት ቀን | 1929 | 44 |
| 14. እንግሊዝ ኢጣልያንን ከኢትዮጵያ ለማስወጣት ወደ ኢትዮጵያ የመጣበት ዘመን | 1933 | 40 |
| 15. ጣልያን ድል የተመታበት ዓመት | 1933 | 40 |
| 16. አቡነ ባስሊዮስ ሊቀ ጳጳስ ሆኑ | 1943 | 30 |
| 17. ኤርትራ ከኢትዮጵያ በፌዴሬሽን ተዋሐደች | 1943 | 30 |
| 18. የሸንቃጤ ረሃብ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን | 1950 | 23 |
| 19. እነጄነራል መንግሥቱ ነዋይ የኃይለ ሥላሴ መንግሥት ለመረንቀል ያደረጉት ሙከራ | 1953 | 20 |
| 20. ኤርትራ ከኢትዮጵያ ተዋሐደች | 1955 | 19 |
| 21. የአፍሪካ አንድነት ድርጅት /አ.አ.ድ./ ተቋቋመ | 1956 | 17 |
| 22. የየካቲት አብዮት መፈንዳት | 1966 | 7 |
| 23. የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከሥልጣን መውረድ | 1967 | 6 |
| 24. የገጠር መሬት የመንግሥት ያደረገው አዋጅ | 1967 | 6 |
| 25. የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት የመንግሥት ያደረገው አዋጅ | 1967 | 6 |
| 26. የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማረፍ | 1967 | 6 |

# በገጠር የሰው ኃይል ጥናት 1973/74

| የመጠይቁ መለያ ቁጥር | 1 | 2 | 3 | | ገጽ 1 | ጥብቅ ምስጢር ለእስታቲስቲክስ ሥራ ብቻ | ፎርም-በገ/የሰ/ኃ/ጥ-1/73-74 የእስታቲስቲክስ ጠቅላይ ጽ/ቤት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 2 | 0 | 2 | | | | |

| 1. ክፍለ ሀገር | 4 | 5 | 2. አውራጃ | 6 | 7 | 3. ወረዳ | 8 | 9 | 4. ገ/ማሕበር ስም | 10 | 11 | 12 | 5. የተመረጠው ቤተ ሰብ መለያ ቁጥር ከፎርም ASS-3 ዓምድ 3 | 13 | 14 | 15 | 16 | 6. የተመረጠው ቤተ ሰብ ተከታታይ ተራ ቁጥር ከፎርም ASS-3 ዓምድ 2 | 17 | 18 | 7. የጥናቱ ዙር | 19 | 8. ቀን | 20 | 21 | 22 | 23 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | 0 | | ወር | | ዓመት | |

| 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 | 21 | 22 | 23 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | ዕድሜያቸው አሥር ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆኑ የቤተሰብ አባላት ብቻ የሚጠየቅ | | | | | ባለፈው 12 ወራት ምርታማ ሥራ ሠራን ላሉት ብቻ የሚጠየቅ | | |
| ተራ ቁጥር | የቤተሰብ መደበኛ አባላት ሙሉ ስም | ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያለው ዝምድና | ጾታ 1= ወንድ 2= ሴት | ዕድሜ | የትውልድ ቦታ | እዚህ ቦታ ያለማቋረጥ የኖሩበት ጊዜ ብዛት በዓመት | የጋብቻ ሁኔታ | የቀለም ችሎታ | የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል | ባለፈው 12 ወራት (ምርታማ) ሥራ ሠርተዋል ? 1= አዎን 2= አልሠራሁም | በዓምድ 19 መልሱ አልሰራሁም ከሆነ ያልሰሩ በት ምክንያት | የሥራ ዓይነት | የቅጥር ሁኔታ | የሚሰሩበት ድርጅት ዋና ምርት ወይም የሚሰጠው አገልግሎት (ኢንዱስትሪ) |
| 24 25 | | 26 | 27 | 28 29 | 30 | 31 32 | 33 | 34 | 35 36 | 37 | 38 | 39 40 | 41 | 42 43 |
| 01 | | | | | | | | | | | | | | |
| 02 | | | | | | | | | | | | | | |
| 03 | | | | | | | | | | | | | | |
| 04 | | | | | | | | | | | | | | |
| 05 | | | | | | | | | | | | | | |
| 06 | | | | | | | | | | | | | | |
| 07 | | | | | | | | | | | | | | |
| 08 | | | | | | | | | | | | | | |
| 09 | | | | | | | | | | | | | | |
| 10 | | | | | | | | | | | | | | |

x= እዚሁ ቦታ የተወለዱ ፤
1= እዚሁ አውራጃ በከተማ ፤
2= እዚሁ አውራጃ በገጠር ፤
3= ከዚሁ አውራጃ ውጭ ፡ በክፍለ ሀገሩ በከተማ
4= ከዚሁ አውራጃ ውጭ ፡ በክፍለ ሀገሩ በገጠር
5= ከዚሁ ክፍለ ሀገር ውጭ ፡ በከተማ
6= ከዚሁ ክፍለ ሀገር ውጭ ፡ በገጠር
7= ከኢትዮጵያ ውጭ

xx ከተወለዱ ጀምሮ
00 ከአንድ ዓመት በታች
01= ከአንድ ዓመት በላይ ከሁለት ዓመት በታች
02 ከሁለት ዓመት በላይ ከሶስት ዓመት በታች
03 ከ3 ዓመት በላይ ከ4 ዓመት በታች
:
98= 98 ዓመትና በላይ

1= አግብተው የማያውቁ
2= በጋብቻ ላይ ያሉ
3= ባለቤታቸው የሞቱባቸው
4= የተፋቱ

1= ማንበብና መጻፍ የሚችሉ
2= ማንበብና መጻፍ የማይችሉ (ማይም)

1= ሥራ አጥ
2= ሥራ ኖሮት በእረፍት ፡ በሕመም ፡ በማምረቻ መሣሪያ መስናከልና በሌሎች ማሕበራዊ ጉዳዮች ምክንያት ያልሠሩ
3= ተማሪ
4= የቤት ውስጥ ሥራ
5= በጡረታ አበል ወይም በሃዋላ የሚኖሩ
6= በእርጅና ምክንያት ያልሠሩ
7= አካለ ስንኩል ስለሆኑ ያልሠሩ

1= ቀጣሪ
2= ተቀጣሪ
3= በግል ሥራ የሚተዳደር
4= ሳይከፈለው ለቤተሰቡ ድርጅት የሚሠራ
5= በሥራ ልምምድ ላይ ያለ

| 24 | 25 | 26 | 27 | 28 | 29 | 30 | 31 | 32 | 33 | 34 | | | 35 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ዕድሜአቸው አሥር ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆኑት የቤተሰብ አባላት ባለፈው ሰባት ቀናት የነበረ የሥራ ሁኔታ | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | አንድ ቀንና ከዚያ በላይ ለሠሩና ሥራ ኖሮአቸው በዕረፍት ላይ ለነበሩ የቤተሰብ አባላት ብቻ የሚጠየቅ | | | | | | | |
| ባለፈው 12 ወራት ከመደበኛ ሥራዎ ሌላ ተጨማሪ ሥራ ለመፈለግ ሙከራ አድርገዋል? 1 = አዎን 2 = አላደረ ግሁም | ሥራ ለመፈለግ ሙከራ ካደረጉ በየትኛው ወራት ነበር ? | ባለፈው ሣምንት (ምርታማ) ሥራ ሠርተዋል? 1 = አዎን 2 = አልሠ ራሁም | በዓምድ 26 መልሱ አዎን ከሆነ የሠሩበት ቀናት ብዛት | በዓምድ 26 ባለፉት ሰባት ቀናት አንድም ቀን አልሠራሁም ካሉ ያልሠሩበት ምክንያት | ሥራ አጥ ከሆኑ በሥራ አጥነት የቆዩበት ጊዜ | የሥራ ዓይነት | የቅጥር ሁኔታ | የሚሠሩበት ድርጅት ዋና ምርት ወይም የሚሰጠው አገልግሎት (ኢንዱስትሪ) | ባለፈው ሳምንት ለሠሩት ያገኙት ክፍያ | የቤተሰብ አባላት ብዛት በጾታ (ከዓምድ 10 እና 12) | | | የቤተሰብ ታተርን (ይህ ዓምድ የሚሞላው በዋናው መ/ቤት ነው) |
| | | | | | | | | | | ወንድ | ሴት | ድምር | |
| 44 | 45 | 46 | 47 | | 48 49 | 50 51 | 52 | 53 54 | 55 56 57 | 58 59 | 60 61 | 62 63 | 64 65 |

1 = ከጥር እስከ መጋቢት
2 = ከሚያዝያ እስከ ሰኔ
3 = ከሐምሌ እስከ መስከረም
4 = ከጥቅምት እስከ ታሕሣሥ
5 = ከጥር እስከ ሰኔ
6 = ከሐምሌ እስከ ታሕሣሥ
7 = ከጥር እስከ ታሕሣሥ

1 = ሥራ አጥ
2 = መደበኛ ሥራ ኖሮት በእረፍት፡በሕመም፡ በማምረቻ መሣሪያ መሠናከልና በሌሎች ማሕበራዊ ጉዳዮች ምክንያት ያልሠሩ
3 = ተማሪ
4 = የቤት ውስጥ ሥራ
5 = በጡረታ አበል ወይም በሀዋላ የሚኖሩ
6 = በእርጅና ምክንያት ያልሠሩ
7 = አካለ ሥንኩል
8 = ጊዜያቱ የእርሻ ወቅት ስላልሆነ ያልሰሩ

1 = ከአንድ ወር በታች
2 = ከአንድ እስከ ሶስት ወር
3 = ከአራት እስከ ስድስት ወር
4 = ከስድስት ወር በላይ

1 = ቀጣሪ
2 = ተቀጣሪ
3 = በግል ሥራ የሚተዳደር
4 = ሳይከፈለው ለቤተሰብ ድርጅት የሚሠራ
5 = በሥራ ልምምድ ላይ ያለ

**36** የገበሬ ማሕበሩ ስም ከፎርሙ ገጽ 1 ዓምድ 4

**37** የተመረጠ ቤተሰብ መለያ ቁጥር ከፎርሙ ገጽ 1 ከዓምድ 5 ይገኛል

**38** የተመረጠው ቤተሰብ ተከታታይ ተራ ቁጥር፡ ከፎርሙ ገጽ 1 ከዓምድ 6 ይገኛል ፡፡

| 39 | ስም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|---|
| መረጃ ሰብሳቢ | | | / / |
| የመስክ ተቆጣጣሪ | | | / / |
| የክፍለ ሀገሩ የእስታቲስቲክስ ተቆጣጣሪ | | | / / |